ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 209 መጋቢት 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## ‹‹የዓባይ ግድብን ዲፕሎማሲያዊ ጫና የተቋቋምነው ኢትዮጵያውያን በጋራ በመቆማችን ነው‹‹

- ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር)
የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪ

**መዓዛ ማሞ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የዓባይ ግድብ ላይ የነበረውን ጫና ተቋቁሞ ግንባታው አሁን ያለበት ደረጃ የደረሰው ኢትዮጵያውያን በጋራ በመቆማችን ነው ሲሉ የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪው ያዕቆብ አርሳኖ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መላው ኢትዮጵያውያን የግድቡ ግንባታ ከጀመረበት ወቅት አንስቶ በገንዘብ እና በሀሳብ ሲደግፉ ቆይተዋል፡፡ ይህም ባለፉት 13 ዓመታት የግድቡ ግንባታ እንዲቆም ሲደረግ የነበረውን ከባድ ጫና ተቋቁሞ ለማለፍ ትልቅ ጉልበት ሆኗል፡፡

በዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ በዓለም አቀፍ ሕግ፣ በውሃ እንዲሁም በግድብ አሠራር የተካኑ ተመራማሪዎች በመመካከር እና በድርድር በመሳተፍ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል ያሉት ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር)፤ መንግሥትም በቁርጠኝነት በግድቡ የግንባታ ሂደት የነበረውን ጫና ለመወጣት ትልቅ ኃይል እንደፈጠረላት አመልክተዋል፡፡

እንደ ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር) ገለጻ፤ በቀጣይም በግድቡ ላይ የሚደረገው ጫና ሙሉ ለሙሉ ሊቆም አይችልም፡፡ የዓባይ ግድብ የኃይል ማመንጫ ግድብ በመሆኑ ውሃው የሚደርስባቸው ሀገራት ሁሉ ቅሬታ ፈጥሮባቸው ነበር፡፡ በተከታታይ በተደረጉ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ቅሬታ

‹‹የዓባይ ግድብን ዲፕሎማሲያዊ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል







## የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ለማሳደግ መንግሥት አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

<u>ቢሾፍቱ</u>:- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት ለሚደረገው ሁሉን አቀፍ ጥረት መንግሥት አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ አስታወቁ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪንና የታንክና ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ማምረቻ ወርክሾፕን ትናንት ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ እንደገለጹት፣ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል ምቹ መሠረተ ልማት አለው። ነገር ግን የሀገር ውስጥ ባለሀብቱና የመንግሥት ተቋማት ያለውን መሠረተ ልማት እየተጠቀሙ አለመሆኑን ገልጸዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን...ወደ ገጽ 5 ዞሯል






## ሀገራዊ ለውጡ በርካታ ገጸ በረከቶችን አምጥቷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ሀገራዊ ለውጡ ለአዲስ አበባ በርካታ ገጸ በረከቶችን አምጥቷል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር ዓባይ ገለጹ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ “ለሀገራችን ብልጽግና በኅብረት እንቆማለን” በሚል መሪ ሀሳብ ባለፉት

ሀገራዊ ለውጡ በርካታ ገጸ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## በዘጠኝ ወር ከ112 ሺህ ቶን በላይ የዓሣ ምርት ተገኘ

- ከሰባት ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በተያዘው የ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ከ112 ሺህ ቶን በላይ ዓሣ ማምረት መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በዘርፉ ለሰባት ሺህ 50 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር

በዘጠኝ ወሩ ከ112 ሺህ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ዜና

# የበልግ ዝናብ የሚቀጥል በመሆኑ ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የበልግ ዝናብ የሚቀጥል በመሆኑ ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፡- የበልግ ዝናብ የሚቀጥል በመሆኑ ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

በሚቀጥሉት የሚያዚያና ግንቦት ወራት የበልግ ዝናብ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተሻለ ጥንካሬ ይቀጥላል ያሉት ዳይሬክተሩ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራል ብለዋል።

በሚቀጥሉት የበልግ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባሕር ወለል ሙቀት ከመደበኛ በላይ ሊሆን እንደሚችል በመግለጽ የሰሜናዊ ሕንድ ውቅያኖስ መደበኛ የባሕር ወለል ሙቀት መጠን ሆኖ ሊቆይ እንደሚችል ጠቅሰዋል።

በሚያዚያና በግንቦት ወራት የበልግ ዝናብ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ በተሻለ ጥንካሬ እንደሚቀጥል ጠቅሰው በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ የምዕራብ ኢጋማሽ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው አስረድተዋል።

ኅብረተሰቡ በቀሪ የበልግ ወራቶች የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚገኘውን የዝናብ መጠንና ስርጭት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ገልጸው በዚህ ወቅት የሚካሄደውን የግብርና እንቅስቃሴዎች፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎችን ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር ማከናወን ያስፈልጋል ብለዋል።

አልፎ አልፎ ከሚኖር ተደጋጋሚ ከባድ ዝናብ ጋር በተያያዘ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ረባዳማ ቦታዎች፣ ወንዝ ዳርና ከተሞች አካባቢ ላይ ሊያደርስ እንደሚችል ጠቅሰው ተፅዕኖውን ለመቀነስ የሚያስችሉ የጥንቃቄ ሥራዎችን ከወዲሁ ማከናወን እንደሚገባ አሳስበዋል።

ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተስተዋለ መሆኑን የገለጹት አቶ ፈጠነ በተለይም 40 በሚደርሱ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 እስከ 96 ሚሊ ሜትር ዝናብ ተመዝግቧል ብለዋል።

በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደነበረ ጠቅሰው ሁኔታው የበልግ የግብርና ሥራን ለማከናወን፣ የተለያዩ ተፋሰሶች የውኃ መጠን እንዲሻሻል፣ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደነበረው ገልጸዋል።

# ፊቼ ጫምባላላ በውስጡ የያዛቸውን የሠላምና አብሮነት እሴቶች ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል

**አመስወርቅ ከበደ**


**አቶ ቀጄላ መርዳሳ**

ሀዋሳ፤ ፊቼ ጫምባላላ በውስጥ የያዛቸውን የሠላም፣ የፍቅርና አብሮነት እሴቶች ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል ሲሉ የባሕልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ ተናገሩ ።

የሲዳማ ዘመን መለወጫ ፊቼ ጫምባላላ በዓል በሀዋሳ ከተማ ትናንት ተከብሯል፡፡ የባሕልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ ፊቼ ጫምባላላ የያዛቸው ዕሴቶች ሳይበረዙ ለትውልድ መሸጋገር አለባቸው። በተለይም በዓሉ በውስጡ የያዛቸው መልካም ዕሴቶች ሳይበረዙ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ መጠበቅና መንከባከብ ይገባል።

ፊቼ ጫምባላላ ከጥንት አባቶች በትውልድ ቅብብሎሽ ተጠብቆ ለአሁኑ ትውልድ የተሸጋገረ ታሪካዊና ባሕላዊ ይዘት ያለው በዓል ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዛሬ ላይ በዓሉ የሲዳማ ሕዝብ ብቻ ከመሆን አልፎ የመላው ኢትዮጵያውያን እና ዓለም ቅርስ ሆኖ መመዝገቡን አውስተዋል። ይህ የሲዳማ ሕዝብ እሴት ትውፊቱን ጠብቆ ለትውልድ እንዲሻገር ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በዓሉ የያዛቸው የሠላም፣ የፍቅርና አብሮነት እሴቶችን ለሀገራዊ የሠላም ግንባታ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን ጠቁመው፤ ይህን በጎ እሴት ለሠላም ግንባታ ማዋል እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

በዘመናት የትውልድ ቅብብሎሽ ዛሬ የደረሰው ፍቼ ጫምባላላ ይዘቱና ከዋኔዎቹ ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ የአሁኑ ትውልድ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበትም ተናግረዋል።

ፊቼ ጫምባላላ የፍቅር፣ የመረዳዳትና የትብብር ተምሳሌት በመሆኑ በሲዳማ ሕዝብ ዘንድ ሁሉም ተከባብሮና ተቻችሎ እንዲኖር አድርጎታል ሲሉም ገልጸዋል።

ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ይህ እሴት ሳይበረዝ ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል የተለያዩ ጥናቶች እያደረገ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ እንደገለጹት፤ የፊቼ ጫምባላላ በዓል የደስታ፣ የኅብረትና ወንድማማችነት እንዲሁም በአዲስ መንፈስ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገሪያ ነው። የሲዳማ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ጠብቆ ያቆየው ይህ በዓል ከልጅ እስከ አዋቂ ሁሉም የሚያከብሩት በዓል ነው።

በዓሉ በውስጡ በርካታ ማኅበረሰባዊ ጠቀሜታ ያላቸው መልካም እሴቶችን የያዘ መሆኑን አንስተው፤ ከዚህ ውስጥ ቂምና በቀልን ትቶ በምሕረትና ይቅርታ መሻገር ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው እንደሆነም ተናግረዋል።

ይህንን መልካም እሴት ማጎልበትና በዕለት ተዕለት መስተጋብር ውስጥ መጠቀም እንደሚገባም አመልክተው፤ የፊቼ ጫምባላላ(አዲስ ዓመት) የስኬት፣ የእድገት እና የድል እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል ።

በበዓሉ ላይ የተገኙት የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው፤ ፊቼ ጫምባላላ በአግባቡ ጠብቆ ማቆየት በመቻሉ የዓለም ሀብት እስከመሆን መድረሱን አውስተው፤ "በውስጡ ያሉ የሠላምና አንድነት ዕሴቶች መንከባከብ ይገባል" ብለዋል።

ፊቼ ጫምባላላ ቂምና ቁሩሾን በመተው ወደ ፊት መጓዝን የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመው፤ ለሠላምና አብሮነት ግንባታ የሚኖረውን ሚና መጠቀም እንደሚገባ ተናግረዋል።

በአንድ ላይ ስንቆም እናተርፋለን፣ በጋራ ስንታይ እንደምቃለን፣ ያለፈውን በይቅርታ ማለፍ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል።

ፊቼ ጨምባላላ የሲዳማ ሕዝብ ለይቅርታ፣ ለእርቅ፣ ለፍቅር እና ለሠላም የሚሰጠውን ከፍተኛ ቦታ የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

በበዓሉ ላይ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገኝተዋል።



# በፍትሕ ሥርዓቱ እየተተገበረ ያለው የለውጥ ፍኖተ ካርታ ውጤት እያስመዘገበ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዳማ፤ በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች እየተተገበረ የሚገኘው የለውጥ ፍኖተ ካርታ አበረታች ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ተገለጸ።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት ከትናንት ወዲያ በተካሄደው ሀገር አቀፍ የሕግ ተርጓሚዎች መድረክ እንደተናገሩት፤ የለውጥ ፍኖተ ካርታ ትግበራ በፌዴራልና በክልሎች እየተሠራበት ይገኛል። ዋነኛ ዓላማው ዜጎች ከዳኝነት አገልግሎቱና ከፍትሕ ሥርዓቱ የሚፈልገውን እርካታ እንዲያገኙ ማድረግ፣ የዳኝነት ነፃነትን ማረጋገጥና በተጓዳኝ ተጠያቂነት ማስፈን ነው።

የለውጥ ፍኖተ ካርታ ትግበራው ግልጸኝነት፤ ፍጥነትና ውጤታማነትና መሰል ዓለም አቀፍ የፍትሕ መለኪያዎች ያካተተ መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህም መመሪያዎችንና ደንቦችን በመፈተሽ የማሻሻልና እንደ አስፈላጊነቱ አዲስ የማውጣት ሥራዎችም እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

የለውጥ ፍኖተ ካርታ ትግበራው ለሦስት ዓመት የሚቆይ መሆኑን ጠቁመው፤ እስካሁን በተከናወኑ ተግባራት በርካታ አበረታች ለውጦችን ማስመዝገብ መቻሉን ተናግረዋል።

ለቀጣይም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኩል ተሠርተው ውጤት ያስመዘገቡ ተግባራትን ለክልሎች የማጋራት ሥራዎች ይሠራሉ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ከዚህ ውስጥ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የተሠራው ድምፅን ወደ ጽሑፍ የሚቀይረው መተግበሪያ ጨምሮ ሌሎችንም ሥራ አቀላጣፊ ተሞክሮዎችና ቴክኖሎጂዎች የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲተግብሯቸው የሚሠራ ይሆናል ነው ያሉት።

የፍርድ ቤቶችን አሠራር ዲጂታል ለማድረግ ከኢንፎርሜሽን ኔትወርክ ደኅንነት አስተዳደር ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት የሚለማው መተግበሪያ በሁሉም ፍርድ ቤቶች ሊያገለግል ስለሚችል ወደ ሥራ ለማስገባት እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

የጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪዚን ፌሎሺፕ ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ፓስተር ዳንኤል ገብረሥላሴ በበኩላቸው ኅብረተሰቡ ፈጣን ፍትሕ ይፈልጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው የፍትሕ ሥርዓት ደግሞ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉበት ነው። በሀገሪቱ ተከስተው የነበሩትና አሁንም በአንዳንድ አካባቢዎች ያሉት ችግሮች ለፍትሕ ሥርዓቱ መጓደል ምክንያት ሆነዋል። በዚህ ሂደት ውስጥም ቢሆን የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ የዳኝነት ሥርአቱ ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል።

በፌዴራልና በክልል እየተተገበረ ያለው የለውጥ ፍኖተ ካርታ እንደ ሀገር ለፍትሕ ሥርዓቱ ውጤታማነት ጉልህ ድርሻ መኖሩን ገልጸው፤ የፌዴራልና የክልል የፍትሕ አካላት በቅንጅት ሊሠሩ የሚያስችላቸው ፕሮጀክት እየተዘጋጀ ይገኛል። ይህ ተጠናቆ መተግበር ሲጀምር በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ትልቅ ለውጥ ማስመዝገብ እንደሚቻልም ገልጸዋል።

"ለውጥ ፍኖተ ካርታ ትግበራው እንደ ክልል በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት አስችሏል" ያሉት ደግሞ የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ደምሴ ዱለቻ፤ እንደ ክልል ለሁለት ዓመታት ማኅበረሰቡን፣ የፍርድ ቤት ሠራተኞችንና በክልሉ ያሉ ጠበቆችን በሙሉ የማወያየት ሥራ መከናወኑንም ጠቅሰዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ በዚህም በርካታ ችግሮች የተነሱ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ተጠያቂነት በአግባቡ አለመኖር ለፍትሕ መጓደል ምክንያት ሆኗል፡፡ ሕዝቡም በፍርድ ቤት ላይ አመኔታ እንዲያጣ ማድረጉ ተለይቷል። ለዚህም የዳኞችን ነፃነት ከማስጠበቅ በተጓዳኝ ተጠያቂነትን የማስፈን ተግባራትንም እያከናወነ ይገኛል።

በተጨማሪ ሀገር አቀፉ የሕግ ተርጓሚዎች መድረክ መካሄዱ ከሌሎች ክልሎችና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሠበሠቡ ግብዓቶች በቀጣይ የለውጥ ትግበራውን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የድጋፍ ሰልፎቹ ለለውጥ ኃይሉ ተጨማሪ የዓላማ ጽናትን የሚያላብሱ ናቸው

ካለንበት ድህነትና ኋላቀርነት መውጣትን ታሳቢ ያደረጉ፤ በብዙ ተስፋዎች ትውልዶችን ያነሳሱ የለውጥ ንቅናቄዎች በተለያዩ ወቅቶች ተካሄደዋል። እነዚህ ለውጦች ደግሞ ተስፋ የተደረገላቸውን ያህል ባይሆንም፣ እያንዳንዳቸው በደግም ይሁን በክፉ፤ በልማትም ይሁን በጥፋት የሚታሰቡ ብሔራዊ ትርክቶችን ፈጥረው አልፈዋል።

በተለይም ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት የነበሩ ትውልዶች፤ ለዘመናዊ ትምህርትና ከዚህ ጋር ተያይዞ ለውጭው ዓለም ከነበራቸው ቅርበት የተነሳ፤ ለሀገራቸው እና ለሕዝባቸው የተሻሉ ነገዎችን ለመፍጠር ባላቸው አቅም ሁሉ ተንቀሳቅሰዋል። ብዙ መስዋዕትነት በመክፈልም ለዓላማቸው የነበራቸውን ጽናት አሳይተዋል።

ይህ በትውልዶች ቅብብሎሽ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ለሀገርና ለሕዝብ ነገዎች ተስፋ የሰነቀ የለውጥ ንቅናቄ፤ የትናንት ስህተቶችን በማረም ሀገራዊ ተስፋዎችን ተጨባጭ ማድረግ በሚያስችል አዲስ የፖለቲካ አሳቤና መነቃቃት ከተጀመረ እነሆ ስድስት ዓመታትን አስቆጠረ።

በሕዝባችን የመልማት እና እንደ ሀገር በጸና የአንድነት መሠረት ላይ የመቀጠል ፍላጎት ላይ የተመሠረተው ይህ አዲስ የለውጥ የታሪክ ምዕራፍ ፤ እንደ ቀደሙት የለውጥ ታሪኮቻችን በአስቸጋሪ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ሀገርና ሕዝብም ብዙ ዋጋ እንዲከፍሉ ያስገደዱ ክስተቶችንም አስተናግዷል።

የለውጡ ሕዝባዊነትም ሆነ ርዕይ ገና ከጅምሩ ስጋት የፈጠረባቸው የውስጥና የውጭ ኃይሎች፤ የሕዝባችንን የቆየ አብሮ የመኖር ባህል፤ በአንድነት ተቻችሎ በፍቅር የመኖር እሴት በማደብዘዝ ፤ ከዛም ባለፈ የሀገርን ህልውና ጭምር አደጋ ውስጥ በከተተ መንገድ በተቀናጀ እና በተናበበ መልኩ ተንቀሳቅሰዋል።

በዚህም ለውጡን የሚገዳደሩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና እና ፖለቲካዊ ስብራቶች ተፈጥረዋል። ከሁሉም በላይ በለውጥ ሰሞን ግርግር የተፈጠሩ የሴራ አካሄዶች ባልተለመደ መልኩ ሀገራዊ ፈተና ሆነው አልፈዋል። ጠባሳቸውም ተስፋ ባደረግናቸው ነገዎቻችን ላይ ጥቁር ጥላ አጥለዋል።

"ግርግር ለሌባ ይመቻል" እንደሚባለው፣ በለውጡ ማግስት የተፈጠሩ የውስጥ ችግሮቻችንን እንደ መልካም አጋጣሚ የተመለከቱ ታሪካዊ ጠላቶቻችንና መለወጣችንን እንደ ስጋት የሚመለከቱ ኃይሎች ዓለም አቀፍ መድረኮችን ሳይቀር ፤ ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም ሀገሪቱን ከጀመረችው የለውጥ ጉዞ ለማሰናከል ረጅም ርቀት ተጉዘዋል።

የነዚህ ኃይሎች የሴራ ጉዞ ሀገር እንደ ሀገር አበቃላት ወደሚል የሚያርት ትርክት ወስዶን የነበር ሲሆን፤ ይህንን የጥፋት ትርክት የመቀልበሱ ትግል መራራ ከመሆን በዘለለ፤ የብዙ ሀገር ወዳድ ዜጎቻችንን ውድ ሕይወት፤ የቀደመውን ዘመን ስለ ሀገር የመሞት ብሔራዊ ክብርን የጠየቀ ነበር።

በዚህም /በብዙ መስዋዕትነት የሀገርን ህልውና እና የሕዝባችንን የመበተን ስጋት መቀልበስ ተችሏል። በዚህ ሂደት ውስጥ የለውጥ ኃይሉ ችግሮችን በጽናት ተቋቁሞ፤ ለውጡን በከፍተኛ ቁርጠኝነት በመምራት፤ ሀገርን እንደሀገር መታደግ በመቻሉ ከፍ ያለ እውቅና ሊቸረው የሚገባ ነው።

እንደሚታወቀው፤ የአመራሩ ቁርጠኝነት እስከ ጦር ሜዳ የዘለቀው፤ የመጨረሻዋን ደቂቃ በተስፋ መጠበቅን፤ ዓለም አቀፍ ሴራዎችን በአግባቡ ተርድቶ ለዚህ የሚሆን ብርታት ፣ የመንፈስ ጽናት እና የመስዋዕትነት ዝግጁነትን የጠየቀ ነበር ።

በተለይም ሀገር በአስቻጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበረችበት ወቅት፤ በኢኮኖሚው ዘርፍ ሀገር እንደ ሀገር የምትቆምበትን ስትራቴጂ በመንደፍ እና በጠንካራ ዲስፕሊን በመተግበር በዓለም ደረጃ እውቅና ያተረፈ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገቡ የችግሮች መደራራብ ዜጎችን የከፋ ዋጋ እንዳያስከፍል አስችሏል።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮም በሀገሪቱ አዲስ የፖለቲካ ሃሳብ ለመፍጠር/ችግሮችን በውይይትና በድርድር የመፍታት የፖለቲካ ባሕል ለመፍጠር የሄደበት ረጅም መንገድ የተጠበቀውን ያህል ውጤት ባያስገኝም አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ በመፍጠር ሂደት ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ነው።

ይሄን እውነት በመገንዘብም፣ አሁን ላይ የሚደረጉ የዜጎች የድጋፍ ሰልፎችም ለዚህ ተግባር ተገቢውን እውቅና ከመስጠት ባለፈ፤ የለውጥ ኃይሉ እንደ ሀገር የተፈጠሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስብራቶችን ማከም የሚያስችል ቁርጠኝነት እንዲፈጥር ተጨማሪ አቅም እና የዓላማ ጽናት የሚፈጥሩለት ናቸው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሸማቹን ሸክም የሚያቀሉ ወሳኝ ርምጃዎች የተወሰዱበት መጋቢት ወር

**በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

የመጋቢት ወር የሸማቾች ቀን የተከበረበት ብቻ ሳይሆን፣ ለሸማቹ ብስራት የተበሰረበት ወር ነው ማለት እችላለሁ። በዚህ ወር ሸማቹን የተመለከቱ ሶስት አበይት ተግባራት የተከናወኑበት ልዩ ወር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። መንግሥት የሸማቹን ወገብ ያጎበጡ ሸክሞችን የሚያቀሉ ርምጃዎችን መውሰድ መጀመሩ የሸማቾችን ተስፋ እያለመለመ ይገኛል። የችርቻሮ ንግድን ለውጭ ኩባንያዎች ለመክፈት መወሰኑ በችርቻሮ ገበያው ላይ ማርሽ ቀያሪ ነው።

ሸማቹ ዋጋ አወዳድሮ፣ ጥራት አማርጦ እንዲሸምት ከማስቻሉ ባሻገር አቅርቦቱን ፍጹም ያሻሽለዋል ተብሎ ይጠበቃል። በአፈታትና በአቦሰጥ የሚመራውን የችርቻሮ ንግድም ያዘምነዋል ተብሎ ይጠበቃል። ሌላው ሰሞኑን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀው ደንብ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የሕብረተሰብ ክፍል ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሚያደርግ ነው። ይህ በተለይ በመሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች ላይ ተጥሎ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያቀል ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አምራቹን ከሸማቹ በቀጥታ ያለ ደላላ ጣልቃ ገብነት ለማገናኘት የሚያስችሉ የመሸጫ መደብሮችን በመስጠቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ሊረጋጋ ችሏል። ቲማቲም ባለፈው ዓመት በዚህ ሰዓት በኪሎ ከ80 ብር በላይ የነበር ሲሆን አሁን ላይ ከ12 እስከ 35 የገባ ሲሆን፣ ሽንኩርት ደግሞ ባለፈው ዓመት በዚህ ሰዓት ከ120 ብር በላይ የነበር ሲሆን አሁን ግን እንደየአካባቢው ከ40 እስከ 60 ብር ይገኛል። ይህ ደላላ ከግብይት ሥርዓቱ ተወግዶ አምራችና ሸማች በቀጥታ ሲገናኝ እንዲሁ ሁለቱም ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያሳያል።

በእህልና ጥራጥሬም አምራቹን ከሸማቹ በቀጥታ መገናኘት ከተቻለ ዋጋውን ማረጋጋትና መቀነስ ይቻላል። የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ባካሄደው ጥናት ምርት ሸማቹ ጋ የሚደርሰው 58 በመቶ ተጨምሮበት ነው። የሚገርመው ይህ ጭምሬ ከአምራቹ ሳይሆን ከደላላውና ከነጋዴው ኪስ ነው የሚገባው። የግብይት ሰንሰለቱ አምራቹንም ሆነ ሸማቹን ተጠቃሚ እያደረገ አይደለም። ለዚህ ነው የሕገ ወጥ ደላላና የስግብግብ ነጋዴ ሲሳይ ነው እየተባለ የሚተቸው።

> በእህልና ጥራጥሬም አምራቹን ከሸማቹ በቀጥታ መገናኘት ከተቻለ ዋጋውን ማረጋጋትና መቀነስ ይቻላል። የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ባካሄደው ጥናት ምርት ሸማቹ ጋ የሚደርሰው 58 በመቶ ተጨምሮበት ነው። የሚገርመው ይህ ጭምሬ ከአምራቹ ሳይሆን ከደላላውና ከነጋዴው ኪስ ነው የሚገባው። የግብይት ሰንሰለቱ አምራቹንም ሆነ ሸማቹን ተጠቃሚ እያደረገ አይደለም። ለዚህ ነው የሕገ ወጥ ደላላና የስግብግብ ነጋዴ ሲሳይ ነው እየተባለ የሚተቸው

መንግሥት አሁንም ደላላውን ከግብይት ሰንሰለቱ የሚያስወጣ ሕግ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል። በዚያ ሰሞን የግብይት ሰንሰለቱ ላይ እንቅፋት በመፍጠር የዋጋ ንረት እንዲባባስ ያደረጉ 790 ደላላዎች ላይ አስተዳደራዊ ርምጃ መወሰዱን፤ በእህልና ጥራጥሬ፣ በአትክልትና ፍራፍሬና በቁም እንስሳት ግብይት ውስጥ የነበሩ ደላላዎችን ፈቃድ በመሰረዝ ከግብይት ሂደቱ እንዲወጡ መደረጉን፤ በቀጣይ የደላላን ጣልቃ ገብነት በዘላቂነት እልባት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገልጾ ነበር። እኛም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን መመሪያውን ከምን አደረስኸው ስንል እንጠይቃለን። የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አርቅቆ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ከተሻሻለ በኋላ ሰሞኑን በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወደ አጸደቀው የአከራይ ተከራይ አዋጅ እንለፍ።

የአከራይ ተከራይ አዋጁ ደግሞ ጨዋታ ቀያሪና የተከራዩን ሸክም የሚያቀልና መብቱን የሚያስከብር ነው። የነፃ ገበያ ሀዋሪያና ደቀ መዝሙር በሆኑት እንግሊዝና አሜሪካ ሳይቀር ነፃ ገበያ ስድ አይለቀቅም። ፈር ሲለቅ መንግሥታት ጣልቃ በመግባት ፈር ያሲዙታል። በዩናይትድ ኪንግደም ለንደንን ጨምሮ በዩናይትድ ስቴትስ ግዛቶች፣ በአውሮፓ በርካታ ሀገራት፣ በላቲን አሜሪካ እንዲሁ በርካታ ሀገራት የአከራይ ተከራይ ሕግ አላቸው። አከራይ ከመሬት ተነስቶ ዋጋ አይጨምር፣ ተከራይ አያስለቅቅም። ከዚህ አልፈው የኪራይ ተመንና የዋጋ ጣራ አላቸው።

በመንግሥት በተለምዶ የኪቤአድና የቀበሌ ቤቶች ኪራይ ዋጋ በተወሰነ ደረጃ የዋጋ ተመን ያላቸው ሲሆኑ፣ ዋጋቸውም ከግል ቤቶች ርካሽ ነው ማለት ይቻላል። በአንጻሩ የግለሰብ ቤቶች ኪራይ ግን ስድ የተለቀቀና ተከራዩን የሚያማርር ነው። በሰበብ አስባቡ ዋጋ በየጊዜው የሚጨመርበት፣ የተከራዩን መብት የማያከብር ነው። አከራይ እንዳሻው ኪራይ የሚጨምርበት፣ ከቤት የሚያስለቅቅበት፣ ከሁሉም በላይ ደላላ ጣልቃ እየገባ ዋጋ የሚተምንበት ተከራዩን ያማረረ ነበር። ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እየጎነቆለ ያለ ቁልፍ ችግር ነበር ማለት ይቻላል። አሁን ግን ምንም እንኳ የዘገየ ቢሆን ይሄን አንገብጋቢ ችግር የሚቀርፍ አዋጅ ጸድቋል።

መንግሥት ጣልቃ ገብቶ የመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋ መናርን ለማስተካከል፣ የቤት ኪራይ ውል በሕግ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችለውንና በአከራይና ተከራይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን አዋጅ፣ ባለፈው መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀደቀ። አዋጁ «የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር» የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ ዓላማው ግልጽና ተገማች የሆነ የመኖሪያ ቤት ኪራይ አስተዳደር፣ እንዲሁም የአከራይና

ወደ 6ኛው ገጽ ዞሯል

ዜና

# ለችግር የተጋለጡ ሕጻናትን ለመደገፍና ለመንከባከብ የሚያስችል ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ሕጻናት በተሟላ መንገድ እንዲያድጉና ለችግር ተጋልጠው ሲገኙም ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የሕጻናት መብት ስርጸትና ስዕብና ቀረጻ ዴስክ ኃላፊ አቶ በለጠ ዳኘ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ሕጻናት በተሟላ መንገድ እንዲያድጉና ለችግር ተጋልጠው ሲገኙም ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው።

የሕጻናትን ደኅንነት ለማስጠበቅ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው፤ መብታቸውን ከማስጠበቅ አንጻርና ለችግር ተጋልጠው ሲገኙም ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘጋጁ የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ፣ መልሶ ማቀላቀል፣ የአደራ ቤተሰብና ሌሎችም ፕሮግራሞች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆናቸውን አስረድተዋል።

እንደ አቶ በለጠ ገለጻ፤ በ2009 ዓ.ም የወጣውን የሕጻናት ፖሊሲ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በፖሊሲና በአሠራር ሥርዓት ደረጃ ያሉ ጉዳዮች የሚዘረጉበት የሕጻናት ጉዳይ ጥበቃና አያያዝ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን፤ ይህም ሕጻናት በቅብብሉ ሥርዓት የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው።

"ሕጻናት የተለያየ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት አላቸው፤ ጥቃት ሲደርስባቸውም የሚያገግሙበት



**አቶ በለጠ ዳኘ**

ማዕከል ያስፈልጋቸዋል" የሚሉት ዴስክ ኃላፊው፤ ለዚህም እራሱን የቻለ ሥርዓት ተዘርግቶ በክልሎች ደረጃም ተግባራዊ እንዲደረግ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የሕጻናት ፓርላማ ከቀበሌ አንስቶ እስከ ሀገር አቀፍ ደረጃ በማቋቋም የሕጻናት ተሳትፎ እንዲያድግ የማድረጉ ሥራ ትኩረት እንደተሰጠው በመጥቀስ፤ ጥቃት ሲደርስባቸውም እንደ ሕግ፣ ጤና፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። ከፍርድ ቤት ጋር በተያያዘ ለሕጻናት ተስማሚ የሆኑ ችሎቶችን የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ሕጻናትን ከመደገፍ አንጻር በተከናወኑ በርካታ ተግባራትና በተገኙ የግንዛቤ መሻሻሎች የሕጻናት ተሳትፎ የጎለበተበት ሂደት መኖሩንም ገልፀዋል። የውጭ ሀገር ጉዲፈቻን በማስቀረት በሀገር ውስጥ የመተካትና ከሕጻናት ስብዕና ቀረጻ ጋር በተያያዘ የሕጻናት የቀን ማቆያዎች መስፋፋት የተገኙ እምርታዎች መሆናቸውን አብራርተዋል።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ለሕጻናት ማሳደጊያ ተቋማት ከሚያደርገው የቁሳቁስ ድጋፎች በተጨማሪ ከሌሎች አካላትም ድጋፎችን እንዲያገኙ የማስተሳሰር ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ነገር ግን የሚፈለገው ሕጻናት በወላጆቻቸው እቅፍ ውስጥ እንዲያድጉ ሲሆን የሕጻናት ማሳደጊያ የመጨረሻው አማራጭ መሆኑን አቶ በለጠ ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሕጻናትን ቁጥር በእውን ማወቅ ባይቻልም በርካታ ሕጻናት በችግር ውስጥ እንደሚኖሩ አንስተው፤ ከዚህ ቀደም በተሠራ ጥናት ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ቁጥር ከአምስት ሚሊዮን በላይ እንደሆነ አስታውቀዋል።

አክለውም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ ጥናቶች ቢከናወኑም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ጥናቶቹ ተቀባይነት አይኖራቸውም፤ የሕፃናቶቹን ቁጥር በእውን በማወቅ ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ እንደሀገር ብሔራዊ ጥናት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

የሕጻናት ጉዳይ የሁሉም ነው፤ ከቤተሰብ ጀምሮ ማኅበረሰቦች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና ሌሎችም ኃላፊነት እንዳለባቸው የገለጹት አቶ በለጠ፤ ሕጻናት ለጉዳት እንዳይጋለጡና መብታቸው እንዲከበር የመጠበቅና የመከላከል ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አሳስበዋል።

## ሀገራዊ ለውጡ በርካታ ገጸ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ስድስት ዓመታት የተገኙ ስኬቶችን ለማስቀጠል ያለመ የድጋፍ ሰልፍ ትናንት ተካሄዷል።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር ዓባይ እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ ከተማ ለውጡን ተከትሎ የተዘረጉ መሠረተ ልማቶች ለከተማዋና ለነዋሪዎቿ በርካታ ትሩፋት አምጥተዋል። የከተማዋን ገጽታ የሚቀይሩ ፓርኮች ግንባታ፣ የመንገድ መሠረተ ልማት ዝርጋታና ማስፋፊያ፣ ሰው ተኮር የሆኑ ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ሌሎች የልማት ሥራዎች የነዋሪውን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ ናቸው።

ሀገራዊ ለውጡ ለአዲስ አበባ በርካታ ገጸ በረከቶችን አምጥቷል። ይህንን ለውጥ የማስቀጠል ኃላፊነታችንን መወጣት ይጠበቅብናል ያሉት ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር፤ በተለይም የኑሮ ውድነትን ለመፍታት ከፍተኛ የገንዘብ ድጎማ በማድረግ ዋጋን የማረጋጋት ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡ በዚህም በርካታ ውጤቶች ተገኝተዋል ።

በትምህርት ቤት ምገባ መርሐ-ግብር በርካታ ተማሪዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸው፤ በየጊዜው የሚደረገው የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍም በምሳሌነት የሚጠቀስ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በቀጣይ በከተማዋ የሚስተዋሉ የልማትና መሰል ችግሮችን ለመፍታት የለውጡ መንግሥት የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ሰልፈኞቹ ይዘዋቸው ከወጡ መልዕክቶች መካከል አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስ ትሆናለች፣ ሠላማችን በእያንዳንዳችን ቤት ናት፣ በለውጡ መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አመራር የኢትዮጵያ ብልጽግና ይረጋገጣል፣ ታላቁ የህዳሴ ግድብ የአንድነታችንና የጥንካሬያችን መገለጫ ነው እና ሀገራችንን ወደ ከፍታ ለማሻገር ከለውጡ አመራር ጋር በጽናት እንቆማለን የሚሉ ይገኙበታል።

በተመሳሳይ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በወላይታ ሶዶና አርባ ምንጭ ከተሞች፣ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ እና በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ ባለፉት ዓመታት በለውጡ መንግሥት የተገኙ ስኬቶችን የሚደግፍ ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ተካሄዷል። የድጋፍ ሰልፉ "ለሀገራችን ብልፅግና በኅብረት እንቆማለን" በሚል መሪ ሀሳብ የተካሄደ ነው።

በወላይታ ሶዶ ከተማ እየተካሄደ በሚገኘው ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ በዞኑ ከሚገኙ የከተማና ወረዳ አስተዳደሮች የተውጣጡ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፈዋል። የሰልፉ ተሳታፊዎች "ሠላማችን የብልጽግናችን መሠረት ነውና ለሀገራችን ሠላም ተያይዘን እንሠራለን"፣ "ኅብረ ብሔራዊነታችንን በማጠናከር ለሁሉም የምትመች ኢትዮጵያን እንገነባለን" የሚሉና ሌሎች መፈክሮችን አሰምተዋል።

በተመሳሳይ በክልሉ በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ከተማ የለውጡ መንግሥት እያስመዘገበ ያለውን ውጤት የሚደግፍ ሕዝባዊ ሰልፍ ተካሄዷል። ሰልፈኞቹ መንግሥት የውስጥና የውጭ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ውጤት ማስመዝገቡን የሚያመለክቱ መፈክሮችንም አሰምተዋል።

## ‹‹የዓባይ ግድብን ዲፕሎማሲያዊ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የነበረባቸውን ማሳመን ተችሏል፡፡

በታላቁ ዓባይ ግድብ ኢትዮጵያ ያካበተችው ልምድ እና የዲፕሎማሲ ችሎታ በቀጣይ በሚገነቡ ሌሎች ግድቦች ሊገጥሙ የሚችሉ ፈተናዎችን ለማለፍ እገዛ እንደሚያደርግ የተናገሩት ዶክተር ያዕቆብ፣ ዲፕሎማሲያችን በሀገር ደረጃ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝና የተደራጀ በመሆኑ ወደ ፊትም ይሄ የዲፕሎማሲ ጥንካሬ የበለጠ ከፍ እያለ መሄድ እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

በቀጣይ በሌሎች ወንዞች ላይ የሚደረጉት ልማቶች በጋራ የውሃ ሀብት የጋራ ተጠቃሚነት መርሕ መቀጠል እንዳለበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የዓባይ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት ባለፈም ለመስኖ፣ ለዓሣ ማጥመድ እና ለመጓጓዣ እንዲሁም ለመዝናኛ ተመራጭ የሚሆን ቦታ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ለአካባቢው የዱር እንስሳትና ሥነ ምሕዳራዊ ሚዛን ለመጠበቅ ትልቅ ሚና ይኖረዋል ተብሏል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም እንደተጀመረ የሚታወስ ሲሆን፤ ዘንድሮም የግንባታው 13ኛው ዓመት በድምቀት መከበሩ የሚታወስ ነው።

## የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ሳማሳደግ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መንግሥት የሀገር ውስጥ ምርትን በስፋት ማምረትና መጠቀም አለብን የሚል እቅድ ይዞ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ተመስገን፣ ለዘርፉ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል። በኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ በስፋት ለመተካት በውስጥ አቅም እያመረተ መሆኑ የሚደነቅ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ የነዳጅ ተሽከርካሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን ለማቆም መንግሥት እየሠራ ነው። ድርጅቱ ከወቅቱ ጋር ለመሄድ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችንና ማሽኖችን መሥራት ይኖርበታል ብለዋል።

ኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት ለሚያደርገው ተግባር አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል ሲሉ አቶ ተመስገን ገልጸዋል።

በድርጅቱ ብዙ የፈጠራ ሥራዎችን አይተናል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ማሽኖችን ወደ ምርት ለመቀየር የሚሠሩ ሥራዎችን አድንቀዋል። በማምረቻ ፋብሪካው ውስጥ የግብርና ምርቶችን ማቀነባበሪያ ማሽኖችን እየተሠሩ ነው። ይህም አርሶ አደሮች ያሉባቸውን ችግሮች የሚቀርፍ ነው፣ እንደ ሀገር ትልቅ ተስፋ መኖሩን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ተቋሙ ከነበረበት ችግርና እዳ እንዲወጣ ብዙ ማሻሻያ መደረጉን ገልጸው፤ በቀጣይ ተቋሙ የሚያመርታቸውን ምርቶች በስፋት መጠቀም የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ድርሻ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮ ኢንጅነሪንግ ትልቅ የሀገር ሀብት ነው ያሉት አቶ ተመስገን፣ መሥራት የሚችል አቅም፣ እውቀትና ማሽን እንዳለው በመግለጽ፤ አቅሙን ይበልጥ ለማሳደግ ተገቢው ድጋፍ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

## በዘጠኝ ወር ከ112 ሺህ ቶን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መቻሉም ተመላክቷል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የዓሣ ሀብት ልማት ዴስክ ኃላፊ ፋሲል ዳዊት (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የዓሣ ሀብት ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት 117 ነጥብ 42 ሺህ ቶን ዓሣ ለማምረት ታቅዶ፤ 112 ነጥብ 85 ሺህ ቶን ዓሣ በማምረት የእቅዱን 96 ማሳካት ተችሏል፡፡

ምርቱ የተገኘው ከሐይቆች፣ ከወንዞች፣ ከኩሬ፣ ከግድቦችና ትንንሽ ውሃ አካላት መሆኑን ገልጸው፤ በዘጠኝ ወሩ ለዓሣ ዕርባታ ምቹ የሆኑ አንድ ሺህ 460 የዓሣ እርባታ ኩሬዎች ተዘጋጅተዋል ብለዋል፡፡

የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በኩሬ፣ በሐይቅና ግድቦች ላይ ከአምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ የዓሣ ጫጩት ስርጭት መከናወኑንም አስረድተዋል፡፡

በሀገሪቷ ለዓሣ እርባታ ምቹ የሆኑ ሐይቆችና ግድቦች ቢኖሩም ምርቱን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አልተቻለም ያሉት ዶክተር ፋሲል፤ የዓሳ ጫጩት፣ የዘመናዊ ማስገሪያ መሳሪያዎች እና ለእርባታ የሚሆን የዓሳ የመኖ አቅርቦት እጥረት ተግዳሮቶች መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

የመበለቻ ቦታዎች እና የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እጥረትም የምርት ሂደቱን ቀልጣፋ እንዳይሆን ማድረጉንም ጨምረው ገልጸዋል።

ያሉትን ችግሮች በመፍታት ምርቱን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የዓሳ ጫጩት የብዜት ማዕከላትን የማቋቋም እና በሥራ ላይ የሚገኙትን ባሕርዳር፣ አርባምንጭ፣ ሀዋሳ፣ ዝዋይ፣ ባቱ፣ ሰበታ ብሔራዊ የዓሳ ምርምርና የዓሳ ጫጩት የብዜት ማዕከላትን የማጠናከር ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

እንደ ዶክተር ፋሲል ገለጻ፣ የዓሣ ጫጩቶችን የማይጎዱና የእርባታ ሂደቱን የማያስተጓጉሉ ዘመናዊ የማስገሪያ መሣሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ አስፈላጊው እገዛ እየተደረገ ነው፡፡ አስጋሪዎችም በሕጋዊ እና በዘመናዊ መንገድ እንዲያጠምዱ ግንዛቤ እየተፈጠረላቸው መሆኑንም አንስተዋል፡፡

ለዓሳ ሀብት ልማት መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶት እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር ፋሲል፤ የዓሳ ሀብት ልማትን በሌማት ቱሩፋት መርሐ ግብሩ እንዲካተት ተደርጎ ክልሎች ዓሣ በስፋት እንዲያመርቱ የማድረግ፣ የማስተዋወቅ፣ የንቅናቄና ልዩልዩ ሥራዎች እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ዓሣ እርባታ በርካታ ገቢ ማመንጨት የሚያስችል ዘርፍ እንደሆነ የገለጹት ዶክተር ፋሲል፤ ሀገሪቱ በቂ የሆነ የውሃ መጠንና ተስማሚ የአየር ንብረት ያላት በመሆኑ ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ በመግባት የዓሣ ምርትና ምርታማነትን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

በዓሣ ልማት የሥራ ዕድልን ከመፍጠር አንጻር በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ለሰባት ሺህ 424 ዜጎች ለመፍጠር ታቅዶ ለሰባት ሺህ 50 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል ነው ያሉት፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የሸማቹን ሸክም የሚያቀሉ ወሳኝ ...

ከ3ኛ ገጽ የዞረ

ተከራይን መብት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚያስተናግድ ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ነው። በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትም ሆነ በዓለም አቀፍ ሕጎች ከሚታወቁ ሰብዓዊ መብቶች መካከል አንዱ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ሲሆን፣ መንግሥት የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ለማሻሻል የተለያየ ጥረት ቢያደረግም ከፍላጎቱ ጋር መጣጣም እንዳልቻለ የሪፖርተር ዘገባ ያመለክታል።

በቤት ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት በመጠቀምም ምክንያታዊ ያልሆነ የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪዎች በሀገሪቱ ከተሞች እየተስተዋሉ መምጣታቸውን፣ በዚህም ሳቢያ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች መቸገራቸውንና ተረጋግተው ኑሯቸውን እንዳይመሩ ማድረጉን፣ በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋ መናር በከተሞች የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት እያባባሱ ከሚገኙ ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ መሆኑ፣ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የመንግሥትን አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ሆኗል። የኪራይ ዋጋ ጭማሪን በተመለከተም በተቆጣጣሪው አካል ከሰኔ 30 ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና የዋጋ ጭማሪ እንደሚደረግ ተገልጿል።

አዋጁ ከመታተሙ በፊት ከፀደቀበት ዕለት ጀምሮ የፀና እንደሚሆን የፍትሕ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቲዮስ (ዶ/ር) አብራርተው፣ አንድ የውል ዘመን ከሁለት ዓመት ሊያንስ እንደማይችል ገልጸዋል። የቤት ኪራይ ውልና ዋጋ እንደ ክልሎች ነባራዊ ሁኔታ መወሰን እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን፣ ይህንንም የሚቆጣጠር በክልል ደረጃ የሚሰየም አካል እንዲኖር መደረጉን ሚኒስትሩ አስረድተዋል። በዚህ መሀል በሁለቱ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩን ተቆጣጣሪው አካል እንደሚመለከተውና ወደ ፍርድ ቤት እንደማይሄድ ገልጸው፣ ይህም የሆነው በመደበኛ የሕግ ሂደት ላይ ጫና እንዳይፈጠር በማሰብ መሆኑን ተናግረዋል።

አዋጁ ስለቤት ኪራይ ሲያብራራ፣ ለመኖሪያ ቤት የሚያገለግል ከአንድ ክፍል ቤት ጀምሮ መሆኑን፣ ለአጭር ጊዜ የኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ማለትም ሆቴል፣ ሪዞርት፣ እንዲሁም አልጋ ቤቶችን እንደሚያካትት ሚኒስትሩ አስረድተዋል። አዲስ የተገነባ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከራይ ቤት የኪራይ ዋጋ በአከራይና በተከራይ ስምምነት የተዋዋይ ውል እንዲፀና ይደረጋል ሲሉ ጌዲዮን (ዶ/ር) ገልጸዋል። ተከራዩ ውሉን ማቋረጥ ቢፈልግ ከሁለት ወራት በፊት ቀድሞ ማሳወቅ እንደሚኖርበት በአዋጁ ላይ የተቀመጠ ሲሆን ቤቱን ተከራይቶ ሲኖር የኪራይ ክፍያውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለ15 ቀናት ካሳለፈና ለሁለተኛ ጊዜ ለሰባት ቀናት ካሳለፈ፣ አከራዩ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል ተደንግጓል። ተከራይ ሊጠየቅ የሚችለው ቅድመ ክፍያም ከሁለት ወራት የቤቱ ኪራይ ዋጋ ሊበልጥ አይችልም።

አከራዩ ቤቱን ለመሸጥ ሲፈልግ ለተከራዩ የማሳወቅ ግዴታ ባይኖርበትም፣ ቤቱን የሚገዛው ግን ውሉ እንዲቀጥል ካልፈለገ ለተከራዩ የስድስት ወራት ጊዜ መስጠት እንደሚኖርበት፣ ለአዲስ ተከራይ ሲያከራይም ከዚህ በፊት ከነበረው የኪራይ ዋጋ በላይ አድርጎ ማከራየት እንደማይችል ተደንግጓል። ነገር ግን ቤቱ የሚተላለፈው በስጦታ ከሆነ የውል ዘመኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውሉ ቀጣይነት ይኖረዋል። በሌላ በኩል ቀደም ሲል ሲከራይ የነበረ የመኖሪያ ቤት ወይም ግንባታው የተጠናቀቀ አዲስ ቤት ያለ አገልግሎት ከስድስት ወራት በላይ እንዲቀመጥ ከተደረገ፣ ቢከራይ አከራዩ ሊከፍል ይችል የነበረውን የኪራይ ገቢ ግብር ተሠልቶ እንዲከፍል ይደረጋል።

የቤት ኪራይ ክፍያን በተመለከተም በባንክ ወይም

> ነፃ ገበያ ማለት በጥቂት የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ወይም ያለ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ገበያውን አቅርቦት እና ፍላጎትን ተከትሎ እንዲመራ መፍቀድ ማለት ነው (ነፃ ገበያ የዋጋ ጉዳይ ብቻ አይደለም)

በሌላ ሕጋዊ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ብቻ እንዲፈጸም በአዋጁ ተደንግጓል። አዋጁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የነበሩ የአከራይ ተከራይ ውሎችን የሚያስቀር አለመሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ አዋጁ ሲወጣ የነበረ ውል እስከ ቀጣዩ ሦስት ወራት ድረስ እንዲመዘገብ ይጠበቃል። ይህን አዋጅ የጣሰ አከራይና ተከራይ የወንጀል ቅጣት እንደማይጣልበት፣ ነገር ግን አስተዳደራዊ ቅጣት እንደሚጣልበት ተገልጿል።

አዋጁ የአከራዩንና የተከራዩን መብት በማጣጣም የሚያስከብር ስለመሆኑ ጠቁመው፣ በሁለቱ መካከል አለመግባባት ካለ በተቆጣጣሪው አካል በሚደረግ አስተዳደራዊ ፍትሕ የሚቀረፍ መሆኑን ሚኒስትር ጌዲዮን (ዶ/ር) አስረድተዋል። አዋጁ የመኖሪያ ቤት ችግር በስፋት በሚስተዋልባቸው ከተሞች ተግባራዊ የሚደረግ ስለመሆኑና ዝርዝር አፈጻጸሙ ግን ለከተማ መስተዳድሮችና ለክልሎች እንደሚሰጥ አመላክተዋል።

መንግሥት የመኖሪያ ቤት ፍላጎትን ለማሟላት ስላልቻለ ቁጥጥሩ ላይ ትኩረት አድርጓል የሚባለው አግባብ አይደለም ያሉት፣ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ፣ በቤት ግንባታ ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ገልጸዋል። አዋጁ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የመንግሥት ሠራተኞችና የከተማ ነዋሪዎች በአሁኑ ወቅት ያጋጠማቸውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ከ25 እስከ 30 በመቶ በላይ ለቤት ኪራይ ማዋል የለባቸውም ያሉት ሚኒስትሯ ጫልቱ ሳኒ፣ አንድ ተከራይ ምንም ዓይነት የዋጋ ጭማሪ ሳይደረግበት በተከራየው ቤት ውስጥ ለሁለት ዓመታት ያህል ተረጋግቶ መኖር እንዲችል አዋጁ መብት እንደሚሰጠው አስረድተዋል። የቀረበው አዋጅ የመኖሪያ ቤቶችን ኪራይ ብቻ የሚመለከት እንደሆነ፣ የንግድ ቤቶችን የኪራይ ዋጋና ውልን በተመለከተ በሂደት እንደሚታይ ሚኒስትሯ ገልጸዋል።

አዋጁ ከመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋና የኪራይ ውል ጋር የተገናኙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት የሚያበጅ ከመሆኑ ባሻገር፣ መንግሥት ከቤት ኪራይ ገቢ ሊያገኝ የሚገባው የኪራይ ግብር በአግባቡ እንዲከፈል በማድረግ የከተሞችን ገቢ ለማሳደግ ያስችላል ብለዋል። ለምክር ቤቱ የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ለዝርዝር ዕይታ ወደ ቋሚ ኮሚቴ ሳይመራ ድምፅ እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን፣ ይህንንም ተከትሎ ረቂቅ አዋጁ በሦስት ድምፀ ተአቅቦ በአብላጫ ድምፅ ፀድቋል።

ሆኖም አዋጁ ዋና የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት አባባሽ የሆነውን የንግድ ሱቅና ሕንጻ ኪራይ አለማካተቱ ሙሉኡ እንዳይሆን አድርጎታልና መንግሥት እንደገና ሊያጤነው ይገባል ስንል በአክብሮት እናሳስባለን። በተረፈ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት በዘላቂነት እንዲፈታ በማዕቀፍ ማየት ይገባል። ሰላምን ማረጋገጥ፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ብልሹ አሠራርንና ሙስናን ማስወገድ፣ ጠንካራ የፊስካል ፖሊሲን በመከተል የፋይናንስ ሥርዓቱን ማረጋጋት፣ አምራቹንና ሸማቹን ይበልጥ በቀጥታ ማገናኘት እና የሕግ የበላይነትን በተለይ በግብይት ሥርዓቱ ማስፈን ይጠይቃል። በተረፈ ለዚህ ሁሉ ችግር ከዳረጉን ክፍተቶች አንዱ ነፃ ገበያን አዛብተንና አዛንፈን ስለ ምንረዳ ነውና ስለ ነፃ ገበያ ምንነትና አንድምታ ነጥቦችን እናነሳሳ።

በ"The Ethiopian Economic View"ድረ ገጻቸው ቢዝነስ ፣ ኢኮኖሚክስና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመጻፍ ፤ ማህበራዊ ሚዲያውን በተለይ ፌስቡክን ለበጎ አላማ በማዋል የሚታወቁት የኢኮኖሚክስ ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ከሞላ ጎደል Progressive Capitalism (ማለትም በመንግሥት ፤ የግል ሴክተሩ እና የምርምር ተቋማት በመቀናጀት ስትራቴጂክ የሆነ አቅም በመፍጠር አቅርቦት እና ፍላጎትን ማቀራረብ ላይ ያነጣጠረ) ሥርዓት ለመተግበር በምትሞክር ሀገር ውስጥ ነፃ ገበያ ስለሆነ ማስገደድ አንችልም የሚሉ መግለጫዎች ፤ ነፃ ገበያ በመሆኑ መብታችን ነው ተባልን የሚሉ ሸማቾች እና ነፃ ገበያ በመሆኑ ዋጋ ተማኝ ነን የሚሉ አምራቾች/ሻጮች ፤ መስማት በጣም እንግዳ ነገር ነው ይላሉ።

ነፃ ገበያ ማለት በጥቂት የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ወይም ያለ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ገበያውን አቅርቦት እና ፍላጎትን ተከትሎ እንዲመራ መፍቀድ ማለት ነው (ነፃ ገበያ የዋጋ ጉዳይ ብቻ አይደለም)። ነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ዋና ተዋናይ የሆኑት ሸማቾች እና አምራቾች/ሻጮች ሌላው ተዋናይ መንግሥት ተቀንሶ ገበያው ላይ የመወሰን መብት እንዲወስዱ የተሰጠ የውክልና አካሄድ ነው። በዜጎች መካከል ያለው የሀብት ክፍፍል ሲዛነፍም ሆነ ፍታሃዊነትን ለመጠበቅ ሲባል ገበያን ለብዙሃን ምቹነት ሲባል በመንግሥት መጎብኘቱ አይቀርም።

ምክንያቱም ነፃ ገበያን ይዞ ብቅ ካለው አዳም ስሚዝ (1723-1790) ጀምሮ ላለፉት 250 ዓመታት ነፃ ገበያ በወረቀት እንጂ በተግባር አሟልቶ መተግበር የቻለ አንድም ሀገር የለም። በዓለም የኢኮኖሚ ታሪክ ውስጥ ነፃ ገበያ ሥርዓት ምናባዊ ነው ተብሎ የሚተችበት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ መተግበር አለመቻሉ ነው። ምክንያቱም መንግሥታት በጥቂቱም ቢሆን ገበያውን ማየት አለመቻላቸው የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ጣልቃ መግባታቸው ወደው ሳይሆን ተገደው ነው።

ሀገራት በተለይ ፖለቲከኞች ነፃ ገበያ ላይ ገደብ ለማስቀመጥ የሚደፍሩበት መሠረታዊ ምክንያት የሚመነጨው ለፖለቲካል ኢኮኖሚው ደህንነት ፤ ፍታሃዊነትን ለመጠበቅ እና የሕዝብ የጋራ መጠቀሚያ ሀብቶችን ለመፍጠር ሲባል ነው። ገበያ ቸል በተባለ ቁጥር የጥቁር ገበያ መፈርጠም ፤ የብቸኛ አምራች እና አቅራቢነት /ሞኖፓል/ ባህሪ መፈጠር እንዲሁም ወደ ኢኮኖሚው ሥርዓት መግባትን ከባድ የማድረግ ልምምድ ስለሚፈጠር ነው ሲሉ ያብራራሉ አቶ ዋሲሁን ።

ሻሎም ! አሜን።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ችግር ጎዳና ያወጣቸው የባህር ኃይሉ ቺፍ ማስተር

**እፀገነት አክሊሉ**

ትላንት በጉርምስናና ጉልምስና እድሜያቸው ላይ ሀገራቸውን በብዙ ያገለገሉ ጀግኖች ዛሬ ላይ ቀን ዘምበል ሲልባቸው፣ ጎንበስ ቀና ይሉላቸው የነበሩ ሁሉ የት እንዳሉ እንኳን አስታውሰዋቸው አያውቁም። ጊዜ እራሱ አድሎ የሚፈጽም እስከሚመስል ድረስ ለሀገር ለወገን ብዙ የዋሉ ሰዎች ሳይከበሩ እሱ እንኳን ቀርቶ አስፈላጊ ነገር ሳይሟላላቸው በአሳዛኝ ሁኔታ እድሜያቸውን ሲጨርሱ ማየት አሳዛኝ ነው። በተለይ እነዚህ የሀገር ባለውለታዎች ሀገርና ሕዝብ ዘንድ ዋጋ ቢስ ሆነው ተስፋ ሲቆርጡ ከመመልከት የከፋ ነገር የለም።

የዛሬ የሕይወት ገጽታ ዓምዳችን ባለታሪክ በእውቀት የገፉ፣ ለትልልቅ ሀገራዊ ኃላፊነቶች ታጭተው በብቃት የተወጡ ናቸው። ሮጠው መሥራት በሥራቸው ያሉትንም በሚገባ መምራት በሚችሉበት ቁመናና የጤና ሁኔታ ላይ ሆነውም ሀገራቸውን በብዙ ያገለገሉ ጀግና ነበሩ። ባገለገሉባቸው ዘመናትም ለብዙዎች ብርሃን መሆን ችለው ነበር። በተለይም እንደ ሀገር ገዝፈን እንታይበት በነበረው ባህር ኃይል ውስጥ የወጣትነት እድሜያቸውን አሳልፈዋል፣ ማሳለፍም ብቻ ሳይሆን ለሀገር አለኝታ የሆኑ ተግባራትንም ፈጽመዋል።

በባህር ኃይል ውስጥ በተሰማሩበት የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ብዙ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች ካልመጡ ሊሰሩ አይችሉም የተባሉ ቴክኒካል ችግሮችን በአስተማማኙ የሙያ ብቃታቸው ሰርተውና ችግሮቹን ፈተው ለተገቢው አላማ እንዲውሉም ማድረግ የቻሉ ናቸው። በዚህም በቅርብም በሩቅም አለቆቻቸው የታመነባቸውና ምስጋናን ያተረፉ ባለሙያ ነበሩ።

ዛሬ ላይ እድሜያቸው ገፍቶ ከሁሉም በላይ ደግሞ ማጣትና የጤና መጓደል ተደራርበውባቸው የሰው እጅ ያዩ ዘንድ ተገደዋል። ይህም ቢሆን ገን ለሀገራቸው የዋሉት ውለታ ምንጊዜ የሚነገር እና ከመቃብራቸው በላይም በጉልህ የሚጻፍ የአንጸባራቂ ታሪክ ባለቤት ናቸው። እኛም ዛሬ በእንግድነት ስናቀርባቸው ተዝቆ ከማያልቀው የሥራና የሕይወት ልምዳቸው ላይ ጥቂቷን ጨልፈን ነው።

ማስተር ቺፍ ዓለም ገብረሥላሴ የተወለዱት ሰባት ቤት ጉራጌ ውስጥ በ1933 ዓ.ም ነው። በወቅቱም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ከብት በማገድ በእድሜያቸው ሊሰሯቸው የሚችሉ ሥራዎችን ሁሉ በማከናወን እስከ ስምንት ዓመታቸው ድረስ በትውልድ መንደራቸው የመኖርን እድል አግኝተዋል። ከስምንት ዓመታቸው በኋላ ግን አዲስ አበባ ከተማ በነበረው ወንድማቸው አማካይነት ዘመናዊ ትምህርትን ተምረው ሀገር ወገናቸውን ይጠቅሙ ዘንድ ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ አደረጉ።

"…….በገጠር ከእናትና አባቴ ጋር ስኖር የማደርገው ነገር ቢኖር ከብቶች ማገድና በምችለው አቅም ቤተሰቤን ማገልገል ብቻ ነው። ኋላ ላይ ግን ታላቅ ወንድሜ አስተምርሃለሁ በማለቱ ምክንያት የስምንት ዓመት ልጅ ሳለሁ አዲስ አበባ ከተማ መጣሁና ትምህርት ቤት ገባሁ" ይላሉ።

በቄስ ትምህርት ቤት የፊደልን ገበታ የተዋወቁት ማስተር ቺፍ ዓለም በሚገባ ፊደሎቹን እየቆጠሩ ማንበብና መጻፍን እየተለማመዱ ሂሳብ ስሌትንም እየሞከሩ ቆዩ። ከዛም የቄስ ትምህርቱ ሲያልቅ አልያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ በሚባል ትምህርት ቤት በመግባት ለሶስት ወራት ያህል ተምረዋል፣ ነገር ግን እንግሊዘኛ ቢማር ነው የሚጠቅመው በመባሉ ምክንያት ወደ ደጃች ገብረማርያም ትምህርት ቤት ተዘዋወሩ።

"…….መጀመሪያ ቄስ ትምህርት ቤት ነው የገባሁት እዛም አማርኛ ነበር የተማርኩት። በጣም ደስ ብሎኝ ያሳለፍኩት የትምህርት ጊዜዬም እሱ ነው፣ ከዛም ወደተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን ለመከታተል በቃሁ" ይላሉ።

ማስተር ቺፍ በወቅቱ ትምህርት ቤት ይቀያይሩ እንጂ ያን ያህል ትምህርት ይጠቅመኛል ብለው የሚያስቡና የሚማሩ እንዳልነበሩ ይናገራሉ፤ ያም ቢሆን ግን ትምህርት ቤት ከመሄድ አልቀሩም። ነገር ግን ትምህርት ቤት መቆየታቸው ያን ያህል የተፈለገውን ለውጥ የሚያመጣ ያልመሰላቸው ወንድማቸው ጎበዝ ተማሪ ይሆኑላቸው ዘንድ በመሻት በቅሎ ቤት አጠገብ ወደሚገኝ አዳሪ ትምህርት ቤት እንዲገቡ አደረጓቸው።

እውነትም የማስተር ቺፍ ዓለም የትምህርት አቀባበል በአንድ ጊዜ ተቀየረ። ትምህርት ወዳድና በቀላሉ ትምህርትን የሚቀበሉ ከጓደኞቻቸው ጋር በእውቀት የሚፎካከሩ በጠቅላላው ጥሩ የሚባሉ ዓይነት ተማሪ ለመሆን ቻሉ። ትምህርት ቤት ውስጥ ከአንዲት አሜሪካዊት መምህርት ጋር በመገናኘታቸው ትምህርትን በጣም እየወደዱ እንደመጡም ራሳቸው ይናገራሉ።

"…….በወቅቱ አሜሪካዊቷ መምህርት በጣም ጎበዝ ከመሆኗና ስታስረዳም ደስ ትል ስለነበር ወደትምህርት ሳበችኝ። ከዛ ሁሉ በላይ ደግሞ በተማሪዎች መካከል ጤናማ የሆነ የእውቀትና የውጤት ፉክክር እንዲኖር በየሳምንቱ ምርጥ ተማሪን ታወጣና ታበረታታ ስለነበር እኔም ከማን አንሼ በሚል መንፈስ በጣም አጠና በክፍል ውስጥም የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ እከታተል ነበር። በጠቅላላው ትጉህ ተማሪ ለመሆን ስለበቃሁ ቢያንስ ከቀዳሚዎቹ እንኳን ባልሆንም መካከለኛ ተማሪ ለመሆን ግን ችያለሁ" ይላሉ።

በዚህ ሁኔታ የስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በቀጥታ ያመሩት ባህር ኃይልን መቀላቀል ነበር። "…ትምህርቴን አቋርጬ ባህር ኃይል የሄድኩበት ዋናም ምክንያት አንደኛ የደሃ ልጅ መሆኔ ነው፣ ቀጥሎም እያደኩ ነው፣ ግን ከሁሉም በላይ ብዙ ልጆች ባሉበት ቤት ውስጥ በድህነት መኖርን ለማምለጥ የተጠቀምኩበት ዘዴ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል" ይላሉ።

እሳቸው ባህር ኃይል የገቡት በስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤታቸው ነበር። አስፈላጊውን ወታደራዊና ባህር ኃይል ለመሆን የሚያበቃውንም ስልጠና በሚገባ አጠናቀው ሥራቸውን እየሠሩ ኑሮን በድል አድራጊነት አሸንፈው ያሰቡበት መድረስ ባይችሉም የወር ደመወዝ ያላቸው ሳይቸገሩ በልተው ጠጥተው የሚያድሩ ለመሆን ግን አስችሏቸዋል።

እሳቸውና ጓደኞቻቸው ባህር ኃይልን ከተቀላቀሉ በኋላ ባህር ኃይል ለመሆን የሚያስቡ ወጣቶች የግድ አስረኛ ክፍልና ከዛ በላይ ያለ የትምህርት ማስረጃን ማቅረብ ነበረባቸው ፤ ያንን የያዙ በርካታ ወጣቶች ባህር ኃይሉንም ተቀላቀሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለማስተር ቺፍ ዓለም ምቾት አልሰጣቸውም። ምክንያቱም እሳቸው እዛው ላይ ትምህርታቸውን ሳያሻሽሉ ከቆዩ ከኋላቸው የመጡ ሰዎች አዛዦቻቸው ሊሆኑ ነው፤ ይህንን ለማስቀረት መማር እንዳለባቸው ይወስናሉ፤ በወቅቱ ግን ወታደር ቤት ባስፈለገ ጊዜ ልማር፣ ይሄንን ላድርግ፣ ያንን እፈልጋለሁ የሚባልበት ስላይደለ ማስተር ቺፍ ተማር የሚለውን ፍቃድ ከአለቆቻቸው እስከሚሰጣቸው ድረስ ብዙ እልህ አስጨራሽ ትግሎች ማድረግ ውጤቱንም ከፍ ባለ ትዕግስት መጠበቅ ነበረባቸው።

የመማር ርሃብ የያዘቻው ማስተር ቺፍ ከብዙ እልህ አስጨራሽ ትዕግሥት እንዲሁም ከአስመራ አዲስ አበባ ድረስ በደረሰ የጽሑፍና የቃል ንግግር ውይይት በኋላ የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን እዛው አስመራ ሆነው እንዲከታተሉ በበላይ ሹማምንቱ ተፈቀደላቸው። ይህንን የሰሙ ቀን ደስታቸውን ዛሬ ላይ ቆመው ሲያስቡት እንባ በዓይናቸው ሙልት ይላል። ደስታቸውን ይዘው ብረትም እንደጋለ የሚለውን ተረትና ምሳሌ እየተናገሩ በፍጥነት ትምህርታቸውን ለመጀመር ወደ ትምህርት ቤት ሄደው ተመዘገቡ።


"……በእውነት የእዛን ቀን የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ ራሱ በጣም ይከብደኛል። ዛሬም ድረስ ሳስበው ሰውነቴ ይረበሻል። ከተፈቀደልኝ በኋላ ለአራት ዓመታት ያህል ደመወዝ እየተከፈለኝ በቤቴ እያደርኩ ብቻ ምን አለፋሽ ዘና ብዬ ትምህርቴን በከፍተኛ ፍላጎት ተምሬ በጥሩ ውጤት ማጠናቀቅ ቻልኩ"ይላሉ።

በወቅቱ የአራት ዓመት ትምህርታቸውን ከቀለም ትምህርት ባሻገር ሙያዊ ወይም ቴክኒካል እውቀትንም የመማር እድል አግኝተው ስለነበር ልክ 12ኛ ክፍልን ሲያጠናቅቁ በዲፕሎማ የመመረቅ እድልን አግኝተው ነበር። ይህ ዲፕሎማ ደግሞ በቴክኒሻንነት የሥራ ዘርፍ ላይ እንዲመደቡ አስቻላቸው። ማስተር ቺፍ ዓለምም አሁን የልባቸው ደረሰ። ከውትድርናው ዘርፍ ወጥተው ወደ ቴክኒካል ባለሙያነት ተሸጋገሩ።

"…….በወቅቱ 12ኛ ክፍል ትምህርቴን በቀለምም በቴክኒክም አጠናቅቄ ዲፕሎማ ይዤ ነው የተመለስኩት። ይህ ደግሞ የሥራ መስኬን እንድቀይር በአየር ኃይል ውስጥም ተፈላጊ ባለሙያ እንድሆን አስችሎኛል ነበር። በወቅቱ የነበረው የእኔ የሥራ ድርሻም ጀነሬተሮች እንዲሁም በአሰብና ምጽዋ ላይ የነበሩትን የሞተር ጀልባዎችና መርከቦች ሲበላሹ መጠገን ነበር" በማለት ይናገራሉ።

በወቅቱም ከምጽዋ አሰብ እንዲሁም ወደ ጦርነቱ ቦታ ምግብ ቁስለኛ እንዲሁም ሌሎች ነገሮች

ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ማስተር ቺፍ ዓለም ገብረሥላሴ


**የመማር ርሃብ የያዘቻው ማስተር ቺፍ ከብዙ እልህ አስጨራሽ ትዕግሥት እንዲሁም ከአስመራ አዲስ አበባ ድረስ በደረሰ የጽሑፍና የቃል ንግግር ውይይት በኋላ የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን እዛው አስመራ ሆነው እንዲከታተሉ በበላይ ሹማምንቱ ተፈቀደላቸው**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ችግር ጎዳና ያወጣቸው የባህር...

ከ7ኛ ገጽ የዞረ



ማስተር ቺፍ ዓለምም ምንም እንኳን ዘመናቸውን ሙሉ ለሀገራቸው የቁርጥ ቀን ልጅ ሆነው በዱር በገደሉ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠሩ ቤተሰባቸውን እያስተዳደሩ ልጆች እያሳደጉ የኖሩ ቢሆንም ዛሬ ላይ በእርጅና ዘመናቸው ግን አለሁ የሚላቸው አላገኙም

የሚጓጓዙት በመርከብ ነበር። በአንድ ወቅት አንዲት መርከብ በሥራ ላይ እንዳለች ሞተሯ ተቃጠለ፤ በዚህ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ መደናገጥ ተፈጠረ። የመደናገጡ ዋናው ምክንያት ደግሞ ሞተሩን ሊሰራ የሚችል ባለሙያ በሥፍራው አለመኖሩ ነበር።

"......ይህች ቀኝ እጅ የሆነች መርከብ ባልታሰበ ሁኔታ ሞተሯ ተቃጠለ። በዚህ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያው ተረበሸ ፤ አዛዦቹ ሁሉ ተደናገጡ፤ ምጽዋ ያሉትም አስመራ ቴክኒሻን ስላላ የጠየቀውን ገንዘብ ከፍላችሁ በአስቸኳይ አሰሩ የሚል ትዕዛዝ ተላለፈ። ነገር ግን በወቅቱ አስመራ ላይ የነበሩት ጣሊያኖች ሀገራቸው ገብተዋል ፤ በጠቅላላው የመርከቧን ሞተር ጠግኖ ወደ ስር የሚያስገባ አልተገኘም " ይላሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ማስተር ቺፍ ዓለም ምጽዋ ባህር ኃይል ውስጥ ብዙም እውቅና ሳይሰጣቸው ተቋሙ ላይ ያሉ ሥራዎችን ብቻ እየሠሩ ቁጭ ብለዋል፤ በወቅቱ ግን የሚሰሩበት የኤሌክትሪክ ክፍል ውስጥ በርካታ ባለሙያዎች ያሉ ቢሆንም ያን ያህል አመርቂ ሥራን የሚሰሩ አልነበሩም። እሳቸውም ከዛ በፊት የሰሯቸው አመርቂ ሥራዎች በመኖሩ እስኪ እሱ ይሥራው ብለው አዲስ አበባና አስመራ ያሉት አለቆቻቸው ተነጋግረው ወሰኑ።

እሳቸውም ትዕዛዙን በመቀበል መጀመሪያ የሞተር ክፍሉ በስዕል ቁጭ ካደረጉት በኋላ ከለአለቃቸው በማሳየት ልሠራው እችላለሁ የሚል ማረጋገጫ ይሰጣሉ፤ ከዚህ በኋላም አለቃቸው ተስማምተው "ቢቃ ሥራው" የሚል ማረጋገጫ ይሰጧቸዋል ፤ በዚህን ጊዜ ማስተር ቺፍ ዓለም በመነቃቃትና ረዳት በመያዝ ሥራውን በከፍተኛ ጥንቃቄ መሥራት ስለመጀመራቸው ያብራራሉ።

"........ሞተሩ በጣም ትልቅ ነው፤ ሥራውም እጅግ ጥንቃቄ የሚሻ እንዲሁም አድካሚ ነበር፤ ነገር ግን በብቃት በመሥራት በመበየድና አስፈላጊው ቦታ ላይ በመግጠም እንዲንቀሳቀስ አደረግኩኝ። ከፍተኛ የሆነ ደስታ ተሰማኝ። አለቆቼም ከሚገባው በላይ ኮሩብኝ። እንደ ሀገርም ችግር ውስጥ ከመግባት ዳንን" ይላሉ።

በመቀጠልም ሌሎች በጣም አስፈላጊ ሥራዎችን ከመስረታቸውም የተነሳ አለቃቸው በሚገባ ስለተማመኑባቸው ሌላ በጣም አስፈላጊ እጅግ ውድና በመጠኑም ግዙፍ ጀኔሬተር እንዲሠሩ ትዕዛዝ ተሰጣቸው። የአለቃቸውን ትዕዛዝም በመቀበል ሥራውን በብቃትና በአንደኝነት አጠናቀቁት።

ማስተር ቺፍ ለባህር ኃይሉም ሆነ ለሀገር ብዙ ውለታን ውለዋል በሙያቸው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በበረሃ ተቃጥለው ብዙ ቁምነገሮችን ሰርተዋል። በዚህ ውለታቸውም በተቋማቸው እስከ ማስተር ቺፍነት የደረሰን ማዕረግ እድገት አግኝተዋል። ማስተር ቺፍ የሰሯቸው ሥራዎች ከማዕረግ በተጨማሪም አዲስ አበባ ከተማ ላይ ዝውውር እንዲያገኙ አድርጓቸዋል።

ከምጽዋ አዲስ አበባ ከተዘዋወሩ በኋላም በባህር ኃይል ውስጥ በሙያቸው ከፍ ያለ አገልግሎትን መስጠት ጀመሩ። በዚህም ብዙ አገልግሎትን ካደረጉ በኋላ በገዛ ፍቃዳቸው ጡረታ ጠይቀው ከተቋሙ በክብር እንደተሰናበቱ ይናገራሉ።

ወዲያውም ሀገሪቱ በመንግሥት ለውጥ ውስጥ ገባች። ይህ ሁኔታ ደግሞ እንደ አብዛኞቹ የቀድሞ የጦር ሠራዊት አባላት ሁሉ ለማስተር ቺፍም የተመቸ አልሆነም። ብዙ የኑሮ ውጣውረድና ችግሮች ደረሱባቸው። አይበገሬው ወታደር ግን ሂልተን ሆቴልን ጨምሮ ሸራተን አዲስ ሆቴልና ሌሎች ቦታዎች ጋር እየተዘዋወሩ በሙያቸው ማገልገለን ተያያዙት።

**የቤተሰብ ሁኔታ**

ማስተር ቺፍ ትዳር የመሠረቱት በቤተሰብ ነው። የወንድሞቻቸው ልጆች ጓደኛ ሆነው ቤት ሲመጡም ነው ከባለቤታቸው ጋር የተዋወቁት ፤ በዚህ ሁኔታ የሚጀምረው ግንኙነታቸው ፤ ወደጓደኝነት አድጎም

ማስተር ቺፍ ለባህር ኃይሉም ሆነ ለሀገር ብዙ ውለታን ውለዋል በሙያቸው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በበረሃ ተቃጥለው ብዙ ቁምነገሮችን ሰርተዋል

ትንሽ ከቆዩ በኋላ በ1956 ዓ.ም ወደ ትዳሩ ዓለም ገቡ። በዚህ ሁሉ የትዳር ዓመታትም ልጆች ወልደው ለመሳም በቅተዋል።

**የብዙዎች የመኖር ተስፋ**

የ"እኛና እነርሱ" ድንበር የሌለው፣ በዘርና በጎሳ የማይገደብ ሰው በሰውነቱ ብቻ የሚለካበት ነው ሰብዓዊ የበጎ አድራጎት ሥራ። የስያሜው መሠረትም ይሄው ነው፤ ሰብዓዊነት-ሰው ለሰው የሚከውነው ክቡር ሥራ ነው። ሰው በመሆኑ ብቻ! በቃ ሌላ ምንም ምክንያት አይሻም። እኛም እንደ ማስተር ቺፍ ዓለም ያሉ በጉርምስናና በጉልምስና እድሜያቸው ወቅት ለሀገር ብዙ ውለታን ያበረከቱ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ቀን ዘንበል ብሎባቸው የተቸገሩ ከችግርም አልፈው ይገቡበት ይጠለሉበት ያጡትን እየሰበሰበ ስለሚያኖረው ባቡል ኸይር በጎ አድራጎት ድርጅት ለማንሳት ነው።

ድርጅቱ በአሁኑ ጊዜ በርካታ አቅመ ደካሞችን ሰብስቦ በማኖር እንዲሁም ሌሎችን ደግሞ በቀን ሁለት ጊዜ መግቦ ወደመኖሪያቸው በመሸኘት በበጎ ሥራው ከፍ ያለ አስተዋጽኦን እያበረከተ ነው።

ማስተር ቺፍ ዓለምም ምንም እንኳን ዘመናቸውን ሙሉ ለሀገራቸው የቁርጥ ቀን ልጅ ሆነው በዱር በገደሉ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠሩ ቤተሰባቸውን እያስተዳደሩ ልጆች እያሳደጉ የኖሩ ቢሆንም ዛሬ ላይ በእርጅና ዘመናቸው ግን አለሁ የሚላቸው አላገኙም። ይህ ሁኔታ ደግሞ እሳቸውም ለበጎ አድራጊዎች እጅ ይሰጡ ዘንድ አስገድዷቸዋል።

ማስተር ቺፍ ስለቤተሰባቸው ስጠይቃቸው ብዙ ደስተኛ አልነበሩም። እሳቸው በማያውቁት ምክንያት ልጆቻቸው እንደ አባት ሊጠይቋቸው ባላቸው ነገርም ስብስብ አድርገው ሊጦሯቸው ፍቃደኛ አልሆኑም። ነገር ግን ብዙ የዋሉላት ሀገር ብዙ ደጋጎችን የማፍራት አቅምም ያላት ናትና ልጆቻቸው የጨከኑባቸውን አባት ባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት ስብስብ አድርጓቸዋል። ሆዳቸው እንዳይርበናቸው፤ ሰውነታቸውን እንዳይበርዳቸው ፤ ማረፍ ሲፈልጉም ያርፉበት ዘንድ መጠለያ አመቻችቶ እየጦራቸው ነው።

".......እዚህ የመጣሁት በግል ችግሬ ምክንያት ነው፤ አንዳንዶቹ መግለጽ ስለማልፈልግ ልለፋቸው። ነገር ግን ልጆቼ ሁለቱ ተድረዋል። እንደውም አራተኛዋ በትዳሯም በሀብትም ጥሩ ላይ ያለች ናት። ወንዱም አዲስ አበባም አሜሪካን ሀገርም ተምሮ ኑሮውንም አሜሪካን ሀገር አድርጎ በጥሩ ሁኔታ እየኖረ ነው። ይህ ቦታ ለእኔ በጣም ጥሩ ነው። ምንም ብስጭት የለብኝም። የማየውም የምሰማውም ክፉ ነገር የለም ፤ እበላለሁ እጠጣለሁ አርፋለሁ፤ አሁን ላይ ዓይኔ አንደኛዋና እግሬ በጣም ያመኛል እነሱን መታከም ብችል በጣም ደስተኛ ነኝ" በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።

# የሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ-

## እያደገ የመጣውን የዘርፉን አቅም ለማላቅ

**ዳግም ከበደ**



የሆቴሎች የኮከብ ደረጃ በዓለም አቀፍ መስፈርቶች ላይ በመመስረት ለእንግዶች እንዲሁም ጎብኚዎች መረጃ የሚሰጥበት ዘይቤ ነው። ማንኛውም ሀገር ላይ የሚገኝ አንድ ሆቴል ባህሪ፣ ለእንግዶች የሚሰጠውን ምቾት፣ ከደህንነት ጋር ያለውን ጥብቅ መርህ እና የንፅህና ደረጃዎች ከሚይዘው የኮከብ ደረጃ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። አገልግሎት ፈላጊዎችም ከዚያ ሆቴል ምን ማግኘት እንደሚችሉ አስቀድመው ለማወቅ ይረዳቸዋል።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት በአንድ ሀገር ውስጥ ብዛት ያላቸው ጥራታቸውን የጠበቁና መመዘኛ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሆቴሎች መኖራቸው የቱሪዝም አቅምን ለማሳደግ፣ የቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመርና በብዙሃን ተመራጭ ለመሆን ያግዛል።

በቅርቡ የቱሪዝም ሚኒስቴር የዓለም ቱሪዝም ድርጅት ያስቀመጣቸውን አስገዳጅ መስፈርቶች ላሟሉ 31 ሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ ውጤታቸውን ይፋ አድርጓል። በ2014 እና 2015 ዓ.ም ምዘና ከተደረገላቸው 64 ሆቴሎች መካከል ሰባቱ ባለ አራት ኮከብነት ደረጃ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ዘጠኝ ሆቴሎች ደግሞ የሦስት ኮከብ ደረጃን ማግኘታቸውን አሳውቋል። አምስት ሆቴሎች ደግሞ የሁለት ኮከብ እና ስምንት ሆቴሎች ባለ አንድ ኮከብነት ደረጃ የተሰጣቸው መሆኑን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ገልጾ ሁለት ሆቴሎች ደግሞ ከደረጃ በታች መሆናቸውን ገልጾ ነበር።

የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ የኮከብ ደረጃው ይፋ በሆነበት ሥነ ሥርዓት ላይ እንዳሉት፤ ምደባው ሆቴሎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው ከማድረግ ባለፈ በቅርበት ካሉ ተፎካካሪ ሀገራት ሆቴሎች ጋር ያላቸውን አቅም በማሳየት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ተናግረው ነበር።

የዝግጅት ክፍላችን የኮከብ ደረጃ ምደባን (star rating) አስመልክቶ ያነጋገራቸው በዘርፉ ለበርካታ ዓመታት የሠሩት ባለሙያና አሁን ደግሞ በደረጃ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተመረጡት የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ አሸናፊ ሙሉጌታ እንዳሉት፤ በዓለማችን ላይ በአገልግሎት ዘርፍ ሰዎች የሚዝናኑባቸው ካፌዎች፣ ሆቴሎች፣ ላውንጆች፣ ሪዞርቶች የየራሳቸው ደረጃ አላቸው።

በተለያዩ ሀገራት ለሆቴል ደረጃዎች እንደሚሰጥ ጠቅሰው፣ ይህም የተለመደ አሠራር መሆኑን ይገልፃሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህን መሰል የሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ የቅርብ ጊዜ ታሪክ መሆኑን አመልክተው፣ ከዚህ ቀደመ ለሁለት ጊዜያት ብቻ የምደባ ሥራው መከናወኑን ተናግረዋል። እነዚህም የተካሄዱት በ2007 እና በ2011 ዓ.ም መሆኑን ይናገራሉ።

‹‹የመጀመሪያዎቹ የኮከብ ደረጃ ምደባዎች ከተካሄዱ በኋላ በድጋሚ ለመስጠት ረጅም ጊዜያትን ወስዷል›› የሚሉት የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንቱ፤ ይህንን ያህል ጊዜ ለመቆየቱ ምክንያቶቹ የኮቪድ ወረርሽኝና በሀገሪቱ የተከሰተው ግጭት መሆናቸውን ይገልጻሉ። እንዲያም ሆኖ ግን በተናጠል አንዳንድ ሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ውጤታቸው ይወጣ እንደነበርም ነው ያመለከቱት። በዚህ መልኩ ኢትዮጵያ ለአገልግሎት ዘርፉ የኮከብ ደረጃ ምደባ በመስፈርቶች ምዘና መስጠት መጀመሯ ተገቢና የወቅቱ አስፈላጊ ርምጃ መሆኑን ይናገራሉ።

አቶ አሸናፊ እንዳብራሩት፤ ለሆቴሎች የኮከብም ምደባ (star rating) ሲካሄድ ወደ አስር መስፈርቶች ገምት ውስጥ ይገባሉ። የመኝታ ክፍላቸው የተሟላ መሆን፣ አጠቃላይ ፅዳት፣ የደህንነት፣ የሠራተኞች እና የልዩ ልዩ የሆቴል አገልግሎቶች አቅም ደረጃ ከግምት ውስጥ ከሚገቡ ነጥቦች መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው።

እነዚህ መስፈርቶች በዋናነት የጎብኚዎችን፣ የደንበኞችንና በሆቴሉ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ሁሉ ያላቸውን ምቾትና በቀዳሚነት ከግምት ውስጥ ያስገባሉ። በእነዚህ መስፈርቶች መሠረት ሆቴሎች ከኮከብ አንድ ጀምሮ በተከታታይ ያሉ ደረጃዎች ይሰጧቸዋል።

በኢትዮጵያም የቱሪዝም ሚኒስቴር በዚህ መንገድ የሆቴሎችን መደባ አድርጓል።

‹‹አንድ ሆቴል ደረጃ ቢኖረውም ባይኖረውም ደንበኞቹን በጥራትና በጥሩ መስተንግዶ ማገልገል ይኖርበታል›› የሚሉት አቶ አሸናፊ፤ ብዙ ሆቴሎች ገና ከጅምሩ የኮከብ ምደባ ይኖራቸዋል ወይም አይኖራቸውም የሚለው ተረጋግጦ ወደ ሂደት እንደሚገባ ይናገራሉ። ባለኮከብ ሆቴሎች ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አውጥተውና የላቀ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት ይዘው እንደሚገቡም ነው ያብራሩት። ሆኖም ማንኛውም ሆቴል አገልግሎቱን በጥራት የሚሰጥ አቋም ኖሮት ሊሰራ እንደሚገባም ያሳስባሉ።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ባለፈው ሳምንት በርከት ያሉ ሆቴሎችን በመገምገም የሆቴሎች የኮኮብ ምደባ ተደርጓል። ሂደቱ ሙያን የተከተለና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። የቱሪዝም ሚኒስቴር በየጊዜው የግምገማ ነጥቦችን በማውጣት በአገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚገኙትን ሆቴሎች ይገመግማል። ከደረጃ ምደባው በፊት ሆቴሎቹ ያሉባቸውን ክፍተቶች በማሳየት ማስተካከያ እንዲያደርጉ ጥቆማም ይሰጣል። ይህ ሂደት ከታለፈ በኋላ ነው ወደ ደረጃ ምደባ የሚገባው።

‹‹የሆቴሎች የኮከብ ደረጃ አሰጣጥ ሙሉ ለሙሉ ዓለም አቀፍ ደረጃን ይከተላል ማለት አይቻልም›› የሚሉት አቶ አሸናፊ፣ በአንዳንድ ሀገራት ያሉ ትላልቅና ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች የሌላቸውን የኮከብ ምደባ በኢትዮጵያ ውስጥ ከዚያ ያነሰ የጥራት ደረጃ ላይ ለሚገኙት ሲሰጥ ይታያል ይላሉ። አሰጣጡ ልምዱ እየዳበረ ሲሄድ እንደሚሻሻል ገልጸው፣ ይህንን ለማሻሻል የቱሪዝም ሚኒስቴር በግምገማና በተከታታይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ለሆቴል ባለንብረቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ መሠረት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ እየሠራ መሆኑን ያብራራሉ።

ዓለም አቀፍ የኮከብ ደረጃ ምደባን ለማግኘት ሆቴሎች መስፈርቱ የሚጠይቀውን ሁሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሆቴሎች ውስኖቹ በእነዚህ መስፈርቶች ላይ ይሠራሉ። በምሳሌነት ባሳለፍነው ሳምንት 60 ከሚደርሱ ሆቴሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ምደባው ግምገማ የደረሱት 31 የሚሆኑት ናቸው። ከ31 ሆቴሎቹ ደግሞ ሁለቱ ከደረጃ በታች መሆናቸው በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይፋ ሆኖ ከምደባው ዝርዝር መውጣታቸውን አቶ አሸናፊ ይገልፃሉ።

ከፍተኛ የሆነ የኮከብ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሆቴሎች በያዙት ምደባ የማይቀጥሉበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል የሚሉት አቶ አሸናፊ፤ የሚሰጡት አገልግሎት በየተወሰኑ

> **ም**ደባው ሆቴሎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው ከማድረግ ባለፈ በቅርበት ካሉ ተፎካካሪ ሀገራት ሆቴሎች ጋር ያላቸውን አቅም በማሳየት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል

ዓመታት ዳግም እየተገመገመ ምደባው ሊስተካከል የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልም ይናገራሉ። በውጤቱም ጥራታቸው የሚወርድ ምደባው ሆቴሎች ዝቅ የሚሉበት ደረጃቸውን ያሻሽሉት ደግሞ ከፍ የሚሉበት እድል እንደሚፈጥር ይገልፃሉ። ሆቴሎችም የውድድር አቅም እንዲፈጥሩ፣ አገልግሎታቸውን በየጊዜው እንዲያሻሽሉ እድል እንደሚፈጥር ያስረዳሉ። የቱሪዝም ሚኒስቴርም በየሶስት ዓመት ልዩነቱ ግምገማ ለማድረግ ማቀዱ ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ።

‹‹ሆቴሎች ዓለም አቀፍ የኮከብ ደረጃ ኖራቸው ማለት በብዙ ነገር ተጠቃሚ ያደርገናል›› የሚሉት አቶ አሸናፊ፤ በተለይ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እንግዶች አገልግሎት ለማግኘት ሲፈልጉ ሆቴሎች ያላቸውን የኮከብ ደረጃ እንደሚያጣሩ ይናገራል። በመሆኑም እዚህ ደረጃ ውስጥ ያሉ ሆቴሎች መኖራቸው ደንበኞች ለደህንነታቸው ስጋት ሳይገባቸው ግልጋሎት ስለሚያገኙ በብዛት ተመራጭ እንደሚያደርጋቸው ይገልፃሉ። እንደ ሀገርም የቱሪስት ፍሰቱ እንዲያድግ የሆስፒታሊቲ ዘርፉ የጥራት ደረጃም የተሻሻለ እንዲሆን ትልቅ እድል እንደሆነ ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትንም ቱሪስቶችን ለመሳብ ትወዳደራለች የሚሉት አቶ አሸናፊ፣ በአምስት፣ አራት፣ ሦስት እና ሁለት ኮከብ ደረጃ በብዛት በአንድ ሀገር ውስጥ ሆቴሎች መኖራቸው ጎብኚዎችንም ለመሳብ የሆስፒታሊቲ ዘርፉን ለማላቅ ያግዛል ሲሉ ያብራራሉ።

አቶ አሸናፊ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ከ360 ወይም 370 የማይበልጡ ሆቴሎች በኮከብ ደረጃ ውስጥ ይገኛሉ። ይህንን ቁጥር በየጊዜው ማሳደግ ሲቻል የቱሪስት ፍሰቱን መጨመርና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖራል። በተለይ በማይስ ቱሪዝም ትላልቅ ኤግዚቢሽኖች፣ ስብሰባዎች እንዲሁም መሰል ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ሁነቶች ሲኖሩ በቀላሉ ጨረታውን ለማሸነፍና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚችል አቅም ለመፍጠር ያግዛል።

በዘንድሮው የቱሪዝም ሚነስቴር የኮከብ ደረጃ ምደባ ላይ ቅሬታዎች መቅረባቸውን የሚናገሩት አቶ አሸናፊ፤ ከተለያዩ የዘርፉ ሙያዎች የተውጣጡ አባላት ያሉት ገለልተኛ ኮሚቴ መቋቋሙን ይናገራሉ። እርሳቸውም በዚህ ኮሚቴ ውስጥ አባል እንደሆኑ ተናግረው፣ ቅሬታዎቹን ለመመልከት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

የሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ በበባህሪው አጨቃጫቂ መሆኑን በመግለፅም ቅሬታዎችን ከመስፈርቶች አኳያ ለመፍታት እንደሚሞክር ተናግረዋል። ብዙ የሆቴል ባለንብረቶች በባለ አምስት ኮከብ ደረጃ ቢመደብላቸው ፍላጎታቸው ነው በማለት የሚያነሱት አቶ አሸናፊ፣ የቅሬታውን ተገቢነት ከመስፈርቱ አንፃር ማጣራት ግን ተገቢ መሆኑን አስታውቀዋል።

‹‹የቀረቡ ቅሬታዎች አሊያም ትችቶች ሁሉ እውነትነት ላይኖራቸው ይችላል›› ሲሉም ጠቅሰው፣ በምደባ ወቅት ስህተቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉም ይገልፃሉ። የገለልተኛ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ቀዳሚ ኃላፊነት ከመስፈርቶቹ አንፃር ለሆቴሎቹ የተሰጡት የኮከብ ደረጃዎች ተገቢነትን በሚቀርበው ቅሬታ ላይ ተመስርቶ ማጣራት እና መፍትሔ መስጠት መሆኑን ያስረዳሉ።

የሆቴሎች የኮከብ ምደባ የተካሄደው ከሳምንት በፊት ነው የሚሉት አቶ አሸናፊ፣ በምደባው ያልተስማሙ ባለንብረቶች ቅሬታቸውን ለኮሚቴው እያስገቡ መሆኑን ይናገራሉ። ለዚህ እልባት ለመስጠት ኮሚቴው ሆቴሎቹ የሚገኙባቸው ቦታዎች በመሄድ የአካል ምልከታና ግምገማ እንደሚያደርግ ይገልፃሉ። በወጤቶቹ መሠረትም ምደባውን ካደረገው የቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመቀመጥ ችግሮች ያሉባቸውን ውሳኔዎች ለመመልከትና ውሳኔ ለመስጠት እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ አሸናፊ የቀድሞው አሠራር ደረጃ መዳቢዎቹ ቀድመው ሆቴሎቹን እንዲያውቁ እድል የሚፈጥር እንደነበር አስታውሰው፣ ይህ አሠራር ለድርድርና ተገቢ ላልሆነ አሠራር ክፍተት የሚፈጥር እንደነበር ያስረዳሉ። አሁን ግን ይህ አካሄድ መቀየሩ ጠቅሰው፣ የቴክኒክ ቡድኑ እስከ ግምገማ ቀኑ ድረስ የት ቦታ እንደሚመደብ እንደማያውቅ ይገልፃሉ። ውሳኔውም ከመስፈርት ውጭ ሊደረግ የሚችል የኮከብ ደረጃ አሰጣጥ ሂደትን እንደሚያስቀር አስረድተዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ



**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ቃለ መሃላ ሲፈጽሙ**

## የዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሹመት

ኢትዮጵያ ከአንድ መንግሥት ወደ ሌላ መንግሥት ለውጥ ስታደርግ ጦርነቶች እንደነበሩ የቆዩ ታሪኮችን የታሪክ ድርሳናት፣ የቅርቦችን ደግሞ በሕይወት ያሉ ሰዎች ይመሰክራሉ። ለ27 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር የቆየው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር (ኢህአዴግ) ሞቅ ቀዝቀዝ ሲሉ የቆዩ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ሲደረጉበት ቆይቷል። ከ2008 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ ግን በተለይም በኦሮሚያና በአማራ ክልል አካባቢዎች ጠንከር ያሉ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች አጋጠሙት። በግንባሩ ሁለት ድርጅቶች (ኦህዴድ እና ብአዴን) አመራሮች የኢህአዴግን ጥፋት በግልጽ የመናገር ምልክቶች ታዩ፤ ይህኔ ሕዝብ ወኔ አገኘ። በመጨረሻም ኢህአዴግ ለ17 ቀናት ያህል በር ዘግቶ መከረ። አራቱ የግንባሩ ድርጅቶች ሊቃነ መናብርት በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ አሉ። «በስብሰናል፣ አጥፍተናል» እያሉ ተናገሩ። በመጨረሻም ለውጥ መምጣት እንዳለበት ታመነ!

እነሆ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተመረጡ! «ፖለቲካና ኤሌክትሪክን በሩቁ» ይባል የነበረው የፖለቲካ ባህል ተቀየረ። መንግሥትን ለመቃወም ሰልፍ ይወጣባቸው የነበሩ አደባባዮች መንግሥትን ለመደገፍ በሚወጣ ሰልፈኛ ተጥለቀለቁ።

ዶክተር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ማግስት ጀምሮ በተለያየ ዘርፍ ውስጥ የሚገኘውን የማህበረሰብ ክፍል ማወያየት ጀመሩ። መምህራንን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ የኪነ ጥበብ ሰዎችን፣ ባለሀብቶችን... በየደረጃው ያለውን የሕብረተሰብ ክፍል አወያይተዋል። በተለያዩ አካባቢዎች እየሄዱም ነዋሪውን አወያይተዋል።

እንዲህ እንዲህ እያለ የቀጠለው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጉዞ እዚህ ደርሶ እነሆ ዛሬ እየታወሰ ነው። ለአሥርት ዓመታት ተቋርጦ የነበረው የኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት፣ እስር ቤት ተረስተው የነበሩ የፖለቲካ አመራሮችና ጋዜጠኞች መፈታት፣ በተቃውሞ ጎራ የነበሩ አካላት ወደ ፍትሕ ተቋማትና ወደ ካቤኔ መግባት፣ ለዓመታት ተረስቶ የነበረው የወደብ ጉዳይ መነሳት፣ አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ ከተማ መሆኗን የሚመሰክሩ ትልልቅ ውብ ፕሮጀክቶች መሠራታቸው... የለውጡን መንግሥት በዚች ስድስት ዓመት ውስጥ ብቻ በታሪክ ሰነድ ውስጥ ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርጉ ናቸው። የተጀመሩት ሲያልቁ ደግሞ የሺህ ዘመናት ደማቅ ታሪክ እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸው።

ያም ሆኖ ግን ባለፉት ዓመታት እጅግ ነውር የሆኑ ክስተቶችም ታይተዋል። አውዳሚ የእርስ በእርስ ጦርነት ተካሂዷል፤ አሁንም እየተካሄደ ነው። ሀገር አቋራጭ አውራ ጎዳናዎች በተደጋጋሚ ተዘግተዋል። የጋዜጠኞች መታሰር እና የፖለቲከኞች «ፍትሕ የለም» ወቀሳ አሁንም አለ።

በጎ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ጥፋቶችንም ታሪክ ያስቀምጣልና አኩሪ ታሪክ ደምቆ እንዲጻፍ ጥረት ይደረግ እንላለን!

## መጋቢት 24 በኢትዮጵያ ታሪክ

**ዋለልኝ አየለ**

ከ13 ዓመታት ወዲህ እና ከ6 ዓመታት ወዲህ መጋቢት 24 ቀን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታሪካዊ ቀን እንዲሆን አድርጎታል። የመጀመሪያው፤ ከ13 ዓመታት በፊት የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት ቀን ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ መሪ ሆነው የተመረጡበት ነው። ሁለቱን ሁነቶች በዝርዝር እናያለን። ከዚያ በፊት የዚህ ሳምንት ክስተት የሆኑ ሌሎች የታሪክ አጋጣሚዎችን እናስታውስ።

ከ94 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ አረፉ። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በፀና ሲታመሙ ልጅ ኢያሱ ሚካኤል እንዲነግሱ ተደረገ። በነበረው የፖለቲካና የሥልጣን ሽኩቻ መጋቢት 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ከሥልጣን ተሽረው ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ነገሡ። ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ሴት የሀገር መሪ ሆነው በታሪክ ውስጥ ይጠቀሳሉ።

ከ133 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 25 ቀን 1883 ዓ.ም የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ባለቤት እቴጌ መነን አስፋው ተወለዱ። በያኔው አጠራር ወሎ ጠቅላይ ግዛት አምባሰል አውራጃ የተወለዱት እቴጌ መነን እናታቸው ወይዘሮ ስህን ሚካኤል ይባላሉ። ወይዘሮ ስህን እና እቴጌ መነን በተሰየሙላቸው ትምህርት ቤቶች በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ።

ከ83 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም በፋሽስቱ ጣሊያን ተይዛ የነበረችው አዲስ አበባ በኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ቁጥር ስር ዋለች።

በጀኔራል ሰር አለን ጎርደን ከኒንግሃም እየተመራ በደቡብ አቅጣጫ፣ በሶማሊያ በኩል፣ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር የኢትዮጵያ አርበኞችን እያገዘ አዲስ አበባን በመቆጣጠር ጣሊያንን ከአዲስ አበባ አስለቀቁ። በሌላ በኩል በዚሁ ቀን፣ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ለአምስት ዓመታት ያህል በስደት የቆዩት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ከምዕራብ አቅጣጫ በኢትዮጵያውያን አርበኞች እና በሜጀር ጀኔራል ኦርድ ቻርለስ ዊንጌት በሚመራው የእንግሊዝ ጥምር ጦር (የጌድዮን ኃይሎች) የፋሽስትን ሠራዊት ድል እያደረጉ ከሱዳን በኦሜድላ በኩል ደብረ ማርቆስ ደረሱ። ለዚህ ውለታው ይመስላል ጀኔራል ዊንጌት አዲስ አበባ ውስጥ በስሙ ትምህርት ቤት ተሰይሞለታል።

በነገራችን ላይ በደርግ ዘመነ መንግሥት የአርበኞች ቀን ይከበር የነበረው መጋቢት 28 ቀን ነበር። ከዚያ በፊት የአርበኞች ቀን ይከበር የነበረው ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ኃይለሥላሴ አዲስ አበባ በገቡበት እና የጣሊያን ወራሪ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ መውጣት በተረጋገጠበት ሚያዚያ 27 ቀን ነበር። ኢህአዴግ ደርግን ካስወገደ በኋላ የአርበኞች ቀን በድጋሚ ሚያዝያ 27 ቀን እንዲሆን ተደርጎ እነሆ አሁንም በዚሁ ቀን ይከበራል።

ከ7 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም ጀግናው አርበኛ ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ አረፉ። ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በግፍ በወረረበት ዘመን ጀኔራል ጃጋማ በ15 ዓመታቸው ዘመቱ። በዚህ በአፍላው የወጣትነት ጊዜያቸው የ3500 አርበኞች አለቃ ነበሩ። በምዕራብ ሸዋ የነበረውን የፋሽስት ጦር ሰቅዘው የያዙት ጀግናው ጃጋማ ኬሎ፤ አምስት ዓመት ሙሉ በጀግንነት ሲጋደሉ ከማሸነፍ በቀር አንዴም ቢሆን ተማርከውም ሆነ ተሸንፈው አያውቁም። በተለያዩ የጦር ውሎዎች ላይ ባደረጉት ተጋድሎ በጠላት ላይ ከፍተኛ ጀብዱን ከመቀዳጀት ባሻገር፤ በርካታ የጣሊያን የጦር አዝማቾችን ማርከው ለጨካኝ ፋሽስቶች የኢትዮጵያውያንን ርህራሄ አሳይተዋል። የማረኳቸውን በርካታ የጣሊያን ጀኔራሎችም ለእንግሊዝ አስረክበዋል።

እኚህን ጀግና አርበኛ፤ በዚሁ በሳምንቱን በታሪክ፣ በባለውለታዎቻችን እና በሌሎች ዓምዶቻችን በተለያየ ዓውድ በዝርዝር ማስነበባችን ይታወሳል።

### ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ

ከ13 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የመሠረት ድንጋዩ ሲያስቀምጡ እንዲህ አሉ። «የሕዳሴ ግድብ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላብ ፊርማ ያረፈበት ነው። » እነሆ ይህ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላብ ዐሻራ



**ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ**

የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያን የጋራ ታሪክ ሆኖ ይታወሳል።

ዕለተ ቅዳሜ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ረፋድ፤ በያኔው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በአሁኑ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ለመላው ኢትዮጵያውያን አንድ ታላቅ ብስራት ተበሰረ። ሀገራዊ አቅምን የሚያሳይ፣ የተፈጥሮ ሀብት ፍትሐዊ ክፍፍልን የሚያስተምር፣ ሰላም እና መተባበርን የሚመሰክር፣ ሕዝባዊ ጥቅምን የማሳየት ዓላማ ያለው፣ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የጥረት ዐሻራ የሚታተምበት፣ ሀገር በአንድ ልብ የሚያስብበትና በአንድ ሳምባ የሚተነፍስበት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሊገነባ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ።

ይህ በኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያውያን የሆነ የሕዳሴ ግድብ እንደሚገነባ ለኢትዮጵያውያን ተበሰረ። ይህን ለዘመናት የማይደፈር መስሎ የኖረ ዓባይ የቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ደፈሩት። በንግግራቸውም እንዲህ አሉ። «... የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላብ ፊርማ ያረፈበት ግድብ በመሆኑ የሕዳሴ ጉዟችን መሐንዲሶች እኛው፣ ግንበኞቹና ሠራተኞቹ እኛው፣ የፋይናንስ ምንጮችና አስተባባሪዎች እኛው፣ በአጠቃላይ የሕዳሴ ጉዟችን ባለቤቶች እኛው መሆናችንን የሚያሳይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታችን ነው።» ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በኋላ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላቡን ፊርማ በማሳረፍ፣ መሐንዲስ፣ ግንበኛና ሠራተኛ፣ የፋይናንስ ባለቤት መሆኑን አረጋገጠ።

የመንግሥት ሠራተኛው ከደመወዙ፣ ነጋዴው ከወረቱ፣ ገበሬው ከምርቱ፣ ተማሪው ከደብተርና እስኪሪቢቶው ወጪውን በመቀነስ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሕዳሴው ግድብ ባለቤት መሆኑን አስመሰከረ። በዓባይ ጉዳይ ላይ ለዘመናት ሲንከባለሉ የኖሩ ጥያቄዎች ምላሽ አገኙ። በቅኝ አገዛዝ ዘመን ዓባይ በኢፍትሐዊ ቦይ እንዲፈስ የተወሰነባቸው ውሳኔዎች በዚያች ዕለት በዚያች ቀን ዋጋ እንደሌላቸው ተረጋገጠ። ስሙ ብቻ የተረፋቸው የናይል ተፋሰስ ሀገሮች አንድም በኢኮኖሚ አቅም ማጣት፣ አንድም በአውሮፓውያን ኢፍትሐዊ ውሳኔ ከደጃቸው ለሚፈሰው ዓባይ ለበርካታ ዘመናት የበይ ተመልካች ሆነው ኖረዋል። ዳሩ ግን የቅኝ አገዛዝ ዘመን አክትሞ፣ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ዘመናቸው አለፈና ዓባይ በፍትሐዊ ቦይ እንዲፈስ ተወሰነ።

ዓባይ በወኔ እና በቆራጥነት እንደሚገነባ የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ በቆራጥ ወኔ ተናገሩ። ያኔ ባረጀ እና ባፈጀ አገዛዝ የነበረው አመለካከት ኢትዮጵያ እንደማትቀበለው ወኔያቸውን አሳዩ። እስኪ በፓርላማው ውስጥ ከተናገሩት ንግግር ደግሞ ይችን እንውሰድ።

«አንዱ የግብፅ ስትራቴጂ ያው ትልቅ ወታደር አስቀ ምጦ ማስፈራራት ነው፤ ይህን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባ ፖሊሲ ቢኖር አለመፍራት ነው።» ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በኢትዮጵያውያን እውን ሆነ። ግብፅ በየጊዜው የምታነሳው እንጉርጉሮ ግድቡን ለሰከንድም እንደማያስቆመው ዳግም ተረጋገጠ። ኢትዮጵያ ሰላማዊ ውይይትን ለዓለም አሳየችበት።

ከዚች ዕለት ጀምሮ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የኔ እያለ የሚጠራው ሆነ። ዓባይ የጋራ መግባቢያ፣ የጋራ ማሰቢያ፣ የጋራ ሀብት ሆነ። ኢትዮጵያ በራሷ አቅም አትገነባውም የሚለው የውስጥ ለውስጥ ሹክሹክታ አንድምታ ሳያገኝ ቀረ። በዓባይ ጉዳይ የመጣ ነገር ሁሉ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ በመሆኑ በጋራ ማዳመጥ ሆነ።

የመገናኛ ብዙኃን ስለ ግድቡ የሚያወሩት ወሬ በሁሉም ሰው ልብ በአንዴ መድረስ ቻለ። ምክንያቱም ስለ ዓባይ ምን ተባለ የሚለው ነገር የሁሉም ሰው ጉጉት ስለሆነ። ይህ ኢትዮጵያንን በአንድ ቋንቋ ያነጋገረ ዓባይ በሁሉም ሰው ልብ ውስጥ የደስታ ምንጭ በመሆን ኩራትን ፈጠረ። ለበርካታ ኢትዮጵያውያንም የሥራ ብቻ ሳይሆን የጥበብ ምንጭ ሆነ። ከተማሪ እስከ ተመራማሪ በዓባይ ላይ ቅኔ በመቀኘት መጠበብ ጀመሩ። ከትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ እስከ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በዓባይ ላይ ምን እንጠበብ በሚል ውስጣቸውን ጠየቁ። በየመድረኮች ዓባይን የሚያመሰግኑ ስንኞች፣ ዓባይን የሚያስውቡ ዜማዎች ተፈጠሩ። ይህም ለበርካታ ወጣቶች እና ተማሪዎች የጥበብ የፈጠራ ምንጭ ሆነ።

ታላቁን የዓባይ ግድብ ከደለል ለመከላከል ሲባል ለበርካታ አርሶ አደሮች ሌላ አጋጣሚ ፈጠረ። ይህም አርሶ አደሮቹ የሚሰሩት እርከን ዓባይን ብቻ ሳይሆን የአርሶ አደሮችን የእርሻ ማሳም አፈሩን በማስቀረት በውሃ እንዳይሸረሸር እስከ ማድረግ ደረሰ።

የመገደቡ ብስራት የተነገረው ዓባይ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ሌላ የይቻላል መንፈስን እና ወኔን ፈጠረ። እንዲያ በአስፈሪነቱ ይመለከበት የነበረው ዓባይ ለካ እንዲህ በሰው ልጅ ቁጥጥር ሥር መዋል ይችላል? የሚል የይቻላል በራስ መተማመንን ፈጠረ። በቃ! የሰው ልጅ የቱንም ነገር መሥራት ይችላል አሰኘ። ግድቡ ከተጀመረ በኋላ ዓባይ የመታየት እና የመጎብኘት ዕድሉ እየጨመረ፤ በስም ብቻ ያውቁት የነበሩ በርካታ ከተሜዎች ዓባይን በአካል ሄዶ የማየት ጉጉት አደረባቸው።

ያኔ ሲጀመር 5250 ሜጋ ዋት ያመነጫል ተብሎ የታሰባው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አቅሙን አሳድጎ ከፍ አድርጓል። ይህ መላው ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመላው ዓለም ሰላም እና አንድነትን እየመሰከረ ያለ ታላቅ ግድብ ሲጠናቀቅ የዓለምን ቀልብ በመሳብ ኢትዮጵያ የዓለም የሰላም ተምሳሌት መሆኗን በተግባር ያረጋግጣል። እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን የሚለው መሪ ቃል ይፈፀምና ሌላ እንድንጀምር ማሳያ ይሆናል።

በቅርቡ ደግሞ ኃይል የመመንጨት ብስራት ጀምሯል። በአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከዓመት በፊት እንደተነገረው፤ ይህ የኢትዮጵያውያን ዐሻራ የሆነው ግድብ የትውልድ ቅብብሎሽ ነው። ያሰቡትን (ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ)፣ የጀመሩትን (አቶ መለስ ዜናዊ)፣ እያስፈጸሙት ያሉትን (ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)) እናመሰግናለን!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## «የአራዳ» ከያኒዋ ድምጻዊት

ቤዛ እሸቱ

የሁለት ሎጋ ጥንዶች ጥምረት የፈጠራት ናትና እሷም ቁመተ ሎጋ ናት፤ ድምጻዊት ዓለም ከበደ። ትውልዷ ከወደ ሰሜን ሸዋ፣ ሸኖ ነው። ቤተሰቦቿ መኖሪያቸውን ወደ አዲስ አበባ መቀየራቸውን ተከትሎ አብዛኛው የልጅነት ትዝታዋ ከዛ ይቀዳል። አዲስ አበባ፣ አማኑኤል፣ ቶታል አካባቢ የልጅነት ትውስታዋ የሙዚቃ ጅማሮዋ ነዋ። ሙዚቃ መስማት ትወዳለች፤ ያም ቢሆን በትምህርት ቤት ቆይታዋ ከሙዚቃ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላት አልነበረችም። ለሁሉም ነገር መጀመሪያ አለውና እሷም በሙዚቃ ሕይወቷ አንድ ብላ ልትጀምር ሠፈሯ የሚገኙትን የቀበሌ ኪነት አባላት ለመቀላቀል ወሰነች።

ወስናም አልቀረች፤ ሠፈሯ ወደሚገኘው የቀበሌ ኪነት ቡድን በማምራት የ"ልቀላቀላችሁ" ጥያቄ አቀረበች። በሚያሰሙት ሙዚቃ ተማርካ የቀበሌ ኪነት ቡድኑን ለመቀላቀል ብታመራም በአቅራቢያዋ የሚገኘው የቀበሌ ኪነት ኃላፊ ልጅነቷን አይተው "በዚህ እድሜሽ አንቺ መሄድ ያለብሽ ወደ ትምህርት ቤት ነው" በማለት ጥያቄዋን ሳይቀበሉ ቀሩ። ቀበሌ እምቢ ስትባል መድረሻዋን ወደ ከፍተኛ ለወጠች። በሠፈሯ ይገኝ ወደነበረው ከፍተኛ ስድስት በማምራት የኪነት ቡድኑን ለመቀላቀል ጥያቄዋን ሠነዘረች። መልሱ የከፋ ሆነ፤ እዚህ የሚገኙት የኪነት አስተባባሪዎች ወላጆቿን በቅርበት ያውቁ ኖሮ ሁለተኛ ትምህርት ትቼ እዚህ አልመጣም እንድትል ከክልከላውም ተጨማሪ ቅጣት ቀጥተው ሸኟት። ለዚህ ምክንያታቸውም "ሕፃን ነሽ፤ ትምህርትሽን ተከታተይ፤ ዘፈኑ የትም አይሄድብሽም፤ ትደርሽበታለሽ።" የሚል ነበር።

በአቅራቢያዋ የሚገኙ የቀበሌም ሆነ የከፍተኛ ኪነቶችን የመቀላቀል ጥረቷ ባይሳካም በሙዚቃ ተስፋ አልቆረጠችም። የሷ ከፍተኛ የተከለከለችውን የሙዚቃ እድል ለማግኘት ወደ ጎረቤት አካባቢዎች አማተረች። በዚህም "ከፍተኛ አምስት" ወደ ተባለ ኪነት ቡድን አቀናች። የምትወዳት የአስቴር አወቀ "ወፌ ላላ" ዘፈን የወጣበት አካባቢ ነውና እሱን ዘፈን ዘፍና የኪነት ቡድኑን ተቀላቀለች። በቡድኑ ከሷ ቀደም ዋና የሴት ድምፃዊያን የነበሩ ቢሆንም፣ እሱን ቦታ ለመውሰድ ጊዜ አልፈጀባትም።

በኪነት ቡድኑ ከዓመት አለፍ ያለ ጊዜ ካገለገለች በኋላ በውድድር አልፉ ማዘጋጃ ቤትን የመቀላቀል እድል አገኘች። አስቴር አወቀ የምወዳት፣ በጣም የምሰማትና ዘፈን ስታወጣ ለመያዝ ጊዜ የማይፈጅብኝ ድምጻዊ ናት በማለት ትገልጻታለች። ማዘጋጃ ቤትን ብትቀላቀልም በመድረክ ሥራዋ አሁንም "ወፌ ላላ"ንና የተወሰኑ የአስቴር ሙዚቃዎችን በመጫወት እንደተገደበች ነው። ምንም እንኳን የምትጫወታቸው ዘፈኖች ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ባህር አቋርጦ ሥራዋን ከማቅረብ አላገዳትም።

በመጀመሪያ የባህር ማዶ ጉዞዋ እስራኤል ሆነ። የማርታ "ዝማሙ፡"፣ የአስቴር አወቀ "ወፌላላ" እና አንድ ሌላ ሙዚቃን ይዛ ባህር ማዶ ተሻገረች። በወቅቱ ድምጻዊ ንዋይ ደበበ በሚያስተባብረው ስብስብ በመካተት እስራኤል ሀገር በሚዘጋጁ የሙዚቃ ኮንሰርቶች ሥራቸውን እንዲያቀርቡ ከታጩ ድምጻዊያን መሃል ሆነች። በስብስቡ ውስጥ አስተባባሪው ንዋይ ደበበን ጨምሮ፤ እውቁ የትግርኛ ቋንቋ ድምጻዊ ኪሮስ ዓለማየሁ፣ ድምጻዊ አረጋኸኝ ወራሽ፣ ድምጻዊ ሰማኸኝ በለው እና ድምጻዊት ቀኑብሽ አበበ ጋር በመሆን ወደ እስራኤል አቀናች።

አብረዋት የተጓዙት አብዛኞቹ የራሳቸው ዘፈን ያላቸው እውቅ ድምጻዊያን ነበሩና በመድረክ ላይ በርካታ ሙዚቃ ከማቅረባቸው ባሻገር ከሕዝቡ የሚያገኙት ፍቅር እኔስ እስከ መቼ በሰው ዘፈን የሚል ስሜት ፈጠረባት። የውጭውን እድል ስታገኝ ከማዘጋጃ ፈቃድ ሳታገኝ ወደ እስራኤል ማምራቷን ተከትሎ ከጉዞዋ ስትመለስ በምሽት ክበቦች ሙዚቃን መሥራት ጀመረች። ሆኖም በሙሉ ባንዶች ታጅቦ መዝፈን የለመደ ልቧ ሊረካ አልቻለም። በዚህ የተነሳ ራስ ቲያትር ባለሙያ ፈልጎ ማስታወቂያ ማውጣቱን ተከትሎ ትያትር ቤቱን ተቀላቀለች።

ራስ ትያትርን መቀላቀሏን ተከትሎ የባህልም ሆነ ዘመናዊ ዘፈኖችን የመጫወት እድል አገኘች። ከዚህ በተጫማሪ በየሳምንቱ በትያትር ቤቱ ይቀርብ በነበረው "ትእይንተ ጥበባት" በተሰኘው መሰናዶ አዳዲስ ሙዚቃዎችን ማቅረብ ጀመረች። በዚህ መድረክ ላይ የባህሉንም ሆነ ዘመናዊ ዘፈኑን በብቃት ማቅረብ በመቻሏ ዓለም የምትሰኝ ድምጻዊ መኖሯን ለማሳወቅ ምክንያት ሆናት። በዚህ የተነሳ "ማህሌት" የተሰኘ ሙዚቃ ቤት የድሮ ዘፈኖችን ሰብስቦ በኮሌክሽን ለማውጣት ሲያስብ ከታጩት መሃል አንዷ ሆነች። እንደልቤ ማንደፍሮ፣ ባህሩ ቃኘው፣ ከተማ መኮንንና እሷ በጋራ ሆነው የሰሩት አልበም ወጣ። አልበሙ ምንም እንኳን ቆየት ያሉ ዘፈኖችን የያዘ ቢሆንም ዓለምን ከአድማጭ ጋር በማስተዋወቅ ረገድ ድርሻው የጎላ ነበር።



ድምጻዊት ዓለም ከበደ

‹‹የሁለት ወንድ ልጆች እናት የሆነችው ድምጻዊቷ በምትኖርበት አሜሪካ፣ ቨርጂኒያ በሚገኙ የሀበሻ ምሽት ክበቦች ሙዚቃን ብታቀርብም በርካታ የሀገራችን የሙዚቃ አድማጮች የሚገኙት በኢትዮጵያ ነውና ከበርካታ አድማጮቿ ተራርቃ ቆይታለች።››

እሷ ከመስፍን ጋር "ሸሞንሟናዬ"ን አንድ የሜሪ አርምዴን "ሞላ ሀገሩ ሰማ" የተሰኘ ሙዚቃ በሷ በድጋሚ ከተዜሙና በአልበሙ ከተካተቱ ሥራዎች መሃል ይገኙበታል። በመቀጠል "አተረማመሰው" ስትል የሰየመችውን አልበም አወጣች። ከዚህ አልበም ውስጥ አተረማመሰው የተሰኘው ዘፈን በምሽት ቤቶች ከፍተኛ ተቀባይነትን ሲያገኝ፣ "በለው በለው" በሀገሪቱ መገናኛ ብዙሃን በብዛት የተሰማ ሥራዋ ነው።

የራሷን ሥራ ማውጣቷን ተከትሎ በየመድረኩ ፈላጊዋ በዛ፤ ሥራዋን ባቀረበችበት መድረክ ሁሉ እሷን የሚሉ አድናቂዎቿ ቁጥር እያሸቀበ ሄደ። ይህን ተከትሎ ከሀገር ውጭም አብረሽን ሥሪ የሚሉ ጥሪዎች በረከቱ። እሷም ለነዚህ ጥያቄዎች ቀና መልስ በመስጠት በመጀመሪያ ጅቡቲ፤ ከጅቡቲ መልስ ወደ ኬንያ በማቅናት የሙዚቃ ሥራዋን አቅርባ ተመለሰች።ወደ ካናዳም ተመሳሳይ የአብረሽን ሥሪ ጥያቄ መምጣቱን ተከትሎ ቀጣዩ መዳረሻዋ ካናዳ ሆነች።

የካናዳ ሥራዋ ሲጠናቀቅ ወደ ጎረቤት አሜሪካ አቅንታ ሥራዋን የምታቀርብበት እድል ተመቻቸ። ከካናዳ ወደ አሜሪካ ስታቀና ሥራዋን አቅርባ ለመመለስ ቢሆንም ለሥራ ያቀናችባት አሜሪካም እስካሁን መኖሪያዋ ሆና ቀርታለች።

መኖሪያዋን አሜሪካ ካደረገች በኋላ "አራዳ" ስትል የሰየመችውን ሦስተኛ አልበም ለአድማጭ አድርሳለች። አልበሙ ላይ የሚገኘው "አራዳ" የተሰኘ ዘፈን በወቅቱ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና በአልበሙ አከፋፋይ አማካኝነት እሷ ወደ ሀገር ቤት ባትመጣም የቀድሞ ቪዲዮቿን ከሀገር ውስጥ የቪዲዮ ምስሎች ጋር በመቀላቀል የቪዲዮ ክሊፕ ተሰርቶላታል።

ይህ ዘፈኗ ለአዲስ አበባ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በከተማው የሚገኙ በርካታ ሠፈሮች የተጠቀሱበት ተወዳጅ ሥራዋ ነው። ሆኖም እሷ ከተጫወተችው በኋላ ድምጻዊ ጎሳዬ ተስፋዬ ዘፈኑን ደግሞ የተጫወተው በመሆኑ የተወሰኑ አካላት የእሱ ሥራ ቢመስላቸውም እውነታው ግን ሙዚቃውን ዓለም ከበደ ቀድማ የሠራችው መሆኑ ነው። የዘፈኑን ሃሳብ ተመስገን ተካ ሲያመጣው ዓለምፀሐይ ወዳጆ ገጣሚነት፤ በታመነ መኮንን የዜማ ደራሲነትና በዓለም ድምጽ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአድማጭ ጆሮ የደረሰ ተወዳጅ ሥራ ነው።

**አራዳ**

እስኪ ላወድሰው
እኔው ላሞጋግሰው
እየደጋገመኝ
ናፈቀኝ አንድ ሰው
ሳሳሁ ኧረ ሳሳሁልህ
እኔስ ገባሁ እዳ
በቆንጆ ልጅ ፍቅር
ሸግዬ የአራዳ (2)
ዛሬም ና ነገም ና
ቢያሻህ ከነገ ወዲያ
እርም ነው ማፍቀሩ
ገላ ከኛ ወዲያ (2)
ብጠራህ አትሰማኝ
ሀገርህ አቀናህ (2)
ፈጥነህ በባቡሩ
በሰጋሩ ናና
ቶሎ ናና ናና
አራዳ ስሙ ሲነሳ
አብረን ፒያሳ ፒያሳ
እንዳያድር ለፊያቱ
ደውልልኝ ከመርካቶ...
ቦሌ ነህ ወይ ሳሪስ ቄራ
ልምጣ በአየር
እንደ አሞራ...
በቅሎ ቤት ነህ
ጌጃ ጎፋ
ምነው ባይህ
ልቤ ጠፋ
ሸሮ ሜዳ
ወይ እንጦጦ
መቼ ቀረ
ልቤ ቆርጦ

የሁለት ወንድ ልጆች እናት የሆነችው ድምጻዊቷ በምትኖርበት አሜሪካ፣ ቨርጂኒያ በሚገኙ የሀበሻ ምሽት ክበቦች ሙዚቃን ብታቀርብም በርካታ የሀገራችን የሙዚቃ አድማጮች የሚገኙት በኢትዮጵያ ነውና ከበርካታ አድማጮቿ ተራርቃ ቆይታለች። ይሄንንም ለመካስ ይመስላል ከበርካታ ዓመታት በኋላና 11 ዓመታትን እንደፈጀ የተገለጸው አራተኛ አልበሟን "አቀላለጠው" በሚል ርእስ ለአድማጭ አድርሳለች። አልበሙ በምትኖርበት አሜሪካ በርካታ የሙያ ባልደረቦቿና አድናቂዎቿ በተገኙበት የ"አልበም ሪሊዝ" ፓርቲ የተደረገለት ሲሆን፣ በአድማጮች ዘንድም ጥሩ ተቀባይነትን አግኝቷል። በሀገር ውስጥ ግን ለረዥም ጊዜ ከአድማጭ ተራርቃ በመቆየቷ ሊሆን ይችላል የተለፋበትን ያህል አልተሰማም።

**አቀላለጠው**

የማምንህ (3)
ወዴት ነህ
ከእንግዲህ ሸብ አድርገው
ድጉን ከወገብህ
ከእንግዲህ አይክፋህ
ዝናር ካጠገብህ
ሸማ ጣል ይሉሃል
ሸማ ጥለህ ውሰድ
አለሁ አትልም ወይ
ጊዜን የመውደድ
ደሞ ደሞ ደሞ ደሞ
ያሸንፋል
ገላህ ቀድሞ
ሸበላ አካልህ
የተመረጠው
ደሞ አንጀቴን አቀላለጠው
አቀላለጠው...
ካንተ አይለየኝ ብዬ
ምያለሁ ከገዳም
አንድም እንደወንድም
አንድም እንደወዳጅ
አምንሃለሁ እንጂ
ምነው አላምንህ
ትረታ የለም ወይ
ስለኔ ሆነህ

የድምጻዊቷ የመጨረሻ ሁለት አልበሞች መኖሪያዋን በሀገረ አሜሪካ ካደረገች በኋላ የተሰሩ ናቸው። የመጨረሻ አልበሟ "አተረማመሰው" 13 ዘፈኖችን የያዘ ሲሆን፤ አልበሙ ከሙዚቃ ሪትም፣ እንዲሁም የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን እንዲያነሱ በማሰብ ጊዜ ሰጥታ መሥራቷን በአንድ ወቅት ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋር በነበራት ቆይታ ገልጻለች። ዓለም ከድምጻዊያን ለአስቴር አወቀ የተለየ ቦታ ያላት ሲሆን፤ ከአስቴር በተጨማሪ ብዙነሽ በቀለ፣ ሐመልማል አባተ፣ ሕብስት ጥሩነህ የምትወዳቸው ድምጻዊያን እንደሆኑ ትናገራለች። ያም ቢሆን የወጣ ካሴት እንደማያልፋትና ሙዚቃ አዳማጭና የበርካታ ድምጻዊያን አድናቂ መሆኗን አትሸሽግም።

# ስፖርት




## በፈተናዎችን ሳትበገር ለድል የበቃችው ቦክሰኛ

ዓለማሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንና የአዲስ አበባ ፖሊስ ክለብ የ66 ኪሎ ግራም የቦክስ ተወዳዳሪዋ ቤተል ወልዴ ውጤታማ ለመሆን ብዙ መሰናክሎችን ማለፍ ነበረባት። ባገኘችው ጠባብ ዕድል ተጠቅማ በጋና አክራ በተካሄደው የአፍሪካ ጨዋታዎች በሴቶች ቦክስ ታሪክ ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያን ለሀገሯ ማስመዝገብ ችላለች። በፍጻሜውም ጨዋታ የሞዛምቢክ አቻዋን ገጥማ 5 ለምንም በሆነ ውጤት ድል አድርጋ ታሪክ ሰርታለች። ከሳምንት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ በተካሄደው የፕሮፌሽናልና ሰሚ ፕሮፌሽናል የቦክስ ውድድርም ተጋጣሚዋን ድል በማድረግ 100 ሺ ብር አሸንፋለች።

የቦክስ ስፖርትን ከመጀመሯ በፊት በሌሎች ስፖርቶች ውጤታማ በመሆን አስመስክራለች። ሀ ብላ መሥራት የጀመረችው የሰርከስ ስፖርት ሲሆን በመቀጠል የውሹ ስፖርትን ተቀላቅላ እየሠራች ወደ ቦክስ ስፖርት ቀልቧ ተስቧል። በውሹ ስፖርት ውጤት እያስመዘገበች የተመለከታት አሰልጣኟ ብቃቷን አስተውሎ እሷ ፍላጎቱ ባይኖራትም የቦክስ ስፖርትን እንድትጀምር ምክር ይለግሳት ነበር።

ቤተል የአሰልጣኛን ምክር ተቀብላ የቦክስ ስፖርት ብትጀምርም፣ እሷ በምትሳተፍበት 66 ኪሎ ግራም (ከባድ ሚዛን) ተወዳዳሪ በማጣት ለብዙ ዓመታት የውድድር እድልን ሳታገኝ ቆይታለች። ፈተናዎች ቢደራረቡባትም ከድል ሊያገዷት አልቻሉም።

በአሰልጣኟ ግፊትና ማባበል በደቡብ ክልል የዞኖች ማጣሪያ ውድድር ተሳትፎ በማድረግ የቦክስ ስፖርት ሕይወትን በወርቅ ሜዳልያ አንድ ብላ ጀምራለች። በቦክስ ውጤታማ እንድትሆን በውሹ ስፖርት የነበራት



ልምድ ነገሮችን ሊያቀልላት ችሏል።

የቦክስ ስፖርት ውስጥ ከፕሮጀክት ጀምሮ 11 ዓመታትን አሳልፋለች። ወላይታ ዞንን ወክላ በዞን ውድድሮች፣ በኋላም ደቡብ ክልልን ወክላ በኢትዮጵያ ቻምፒዮና ተጫውታለች። በወቅቱ በነበረ ምልመላ ወርቅ በማስመዝገብ አካዳሚ መግባት ችላለች። የአካዳሚ ቆይታዋን ከጨረሰች በኋላም ኒያላ ቦክስ ክለብን ተቀላቅላ ለሶስት ዓመታት ቆይታ ከዛም የአዲስ አበባ ቦክስ ክለብ ተፋላሚ ሆናለች።

አሁን ውጤታማ የሆነችበትን ቦክስ ጨምሮ በቴኳንዶ፣ ውሹ፣ ኪክ ቦክስና ሞይንታይ ስፖርቶች ቀበቶና 68 የወርቆ ሜዳልያዎችን ማጥለቅ ችላለች። ሁሉም ስፖርቶች ላይ ስኬታማ እንደነበረችና በአንድ አጋጣሚ በቦክስ ኪሎ ቀንሳ ተጫውታ ከመሸነፍ ውጭ የወርቅ ሜዳልያና የቀበቶ ባለቤት እንደሆነች ትናገራለች።

ቤተል በሌሎቹ ስፖርቶች ውጤታማ መሆኗ ለቦክስ ስፖርት ውጤታማነት ትልቅ አቅም እንደሆናት ታምናለች። ወላጅ አባቷን በልጅነቷ ያጣችው ብርቱዋ ቦክስኛ የእናቷ ድጋፍ ልዩ እንደሆነና ለውጤት እንድትበቃም ረድቷታል።

ከሀገር ወጥታ የመወዳደር ብቃት ቢኖራትም ብዙ እድሎች አምልጧታል። ይህም የሆነው እሷ የከባድ ሚዛን ተወዳዳሪ በመሆኗና ሌላ የከባድ ሚዛን ተወዳዳሪ ቦክስኛ ባለመኖሩ ለመምረጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ነበር። ቦክሰኞች የሚከፈላቸው ክፍያ አናሳ በመሆኑና ከስፖርቱ የሚገኝ የድካም ዋጋ እምብዛም በመሆኑ ተስፋ በመቁረጥ ከስፖርቱ ስለሚወጡ በሚፈለገው ሚዛን ቦክሰኞችን ማግኘት አይቻልም።

ቦክሰኛዋ አድካሚውን የቦክስ ልምምድ አድርጋ ከጨረሰች በኋላ በከባድ ሚዛን ተጨዋች ማጣቱ ብዙ ፈትኗታል። ይህ ደግሞ ካላት ብቃት አኳያ በብሔራዊ ቡድን እድል አግኝታ እንዳትወዳደርና ህልሟን እንዳትኖር እንዳደረጋት በቁጭት ትናገራለች።

ለብሔራዊ ቡድን ለመመረጥ በሪንግ ውስጥ የእሷን ብቃት መለካት ግዴታ በመሆኑና ውድድር በማጣት መጥፎ ስሜት ውስጥ የገባችበትም ወቅት ቢኖርም አንድ ቀን እንደሚሳካ ተስፋ ነበራት። የውድድር ማጣትንና ሌሎች ጫናዎችን ተቋቁማ ለውጤት ልትበቃ ችላለች። ልምምዷን ሳታቋርጥ ለኦሊምፒክ ማጣሪያ እድሏን ለመሞከር ደብዳቤ ጽፋ ወደ ፌዴሬሽን ያመራችው ቤተል፣ በስፖርቱ የቆየችበትን ረጅም ጊዜና ድካም ተመልክተው በብሔራዊ ቡድን የመሳተፍ እድልን በልዩ ሁኔታ ብሔራዊ ቡድኑን ታቅፋ ለውጤት እንድትበቃ አድርጓታል።

የልፋቷን ዋጋ ባገኘችው ውጤት እንደተካሰችና ተጫዋች ለማግኘት ኪሎ በማውረድ ትጨወት እንደነበር የምታስታውሰው ቤተል፣ ለዚህ የማሸነፍ ስነ ልቦናን መላበስ ዋንኛ ማሳሪያዋ መሆኑን ታስረዳለች። ለውድድሩ የነበረው የመዘጋጃ ጊዜ አጭር ቢሆንም የተሰጠው የተመጠነ ስልጠናና የልዑካን ቡድኑ ጥሩ መንፈስ ለድሉ አስተዋጽኦ አድርጓል ትላለች።

በዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ስታደርግ የአፍሪካ ጨዋታዎች የመጀመሪያ እንደመሆኑ እንግዳ ቢሆንባትም እሷ ትኩረትና ሃሳባን ፍልሚያዋ ላይ ብቻ እንዳደረገች ታስታውሳለች። በዚህም ረጅም ዓመት በቦክስ ውስጥ የቆየችበትን ልምድ ተጠቅማ በራሷ መንገድ ለመጫወት ወስና ወደ መፋለሚያ ሪንጉ ገብታለች። የነበራትን የማሸነፍ አቅምንና የተሰጣትን ጠባብ እድል ተጠቅማ ለነገ እድል መክፈት እንዳለባት አስባ በትልቅ ሞራል ድልን ተቀዳጅታለች።

የቦክስ ስፖርት በሕይወቷም ላይ ጠንካራ እንድትሆን በማድረጉ ሰዎች ከሚሏት ነገር በላይ በመሆኑ ፈተናዎችን ተቋቁማ ለውጤት ልትበቃ ችላለች። ‹‹ሴት ልጅ የትኛውንም ተጽዕኖ ተቋቁማ ማንኛውንም ነገር ማሳካት እንደምትችል እኔ ምስክር ነኝ›› ስትልም ተናግራለች።

የጥንካሬ ተምሳሌቷ እንስት ቦክሰኛ፣ የታላቁ ቦክሰኛ ማሃመድ አሊ ሴት ልጅ የሆነችው ላኢላ አሊም አድናቂ ናት። ፍቅረማርያም ያደሳና ሌሎች የሀገር ውስጥ ቦክሰኞችን አርአያ በማድረግ ለውጤት መብቃትን የምትናገረው ቤተል፣ ከልጅነት ጀምሮ ህልሟ በሆነው የኦሊምፒክ መድረክ ተሳትፋ ውጤት ለማስመዝገብ ጠንክራ እየሠራች እንደምትገኝም ጠቁማለች።




# ከ"ንቦችና ዝንቦች" ታሪክ እንማር

እየሩስ ተስፋዬ

ሠላም ልጆችዬ እንዴት ናችሁ? ደህና እንደሆናችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። በትምህርታችሁም ጥሩ ውጤት ለማምጣት በጣም እየጣራችሁ እንደሆነ ጥርጥር የለኝም።

መቼም ልጆችዬ መልካም የሚባሉ ነገሮችን ለመማር ብዙ አማራጮች እንዳሉ ታውቃላችሁ አይደል? ጎበዞች። ለዛሬ አንድ ጥሩ መልዕክት ያለው ታሪክ እናቀርብላችኋለን። ርዕሱ ንቦችና ዝንቦች ይሰኛል። የጻፉት ደግሞ ንጉሥ አየለ ተካ ይባላሉ ። ሙሉውን ታሪክ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል።

ሰዎች የንቦችን ኅብረት ጥበብና ሠራተኝነት የሰሙ ሁለት ዝንቦች በንቦች ቅናት አደረባቸው። አንድ ቀን እንደ አጋጣሚ ሁለት ዝንቦች ጎን ለጎን በጫካ ውስጥ ሲበሩ በርቀት ሁለት ንቦች በዝግታ ሲበሩ አይተው በፍጥነት ደረሱባቸው። ወዲያው ከዝንቦቹ አንዱ ወደ ንቦቹ ጠጋ አለና "እንደምን ዋላችሁ?" ብሎ ሰላምታ አቀረበላቸው። ንቦቹም በትሕትና ለሰላምታው መልስ ሰጡ።

"እባካችሁ የምናማክራችሁ ጉዳይ ስላለን አንድ ጊዜ እዚች ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ አረፍ ብለን እንወያይ?" ብላ ከፊት በኩል ያለችው ዝንብ ንቦቹን ጠየቀቻቸው። ንቦቹም "አይ ቆሞ ለማውራት እንኳ ጊዜ የለንም። እንቸኩላለን። ግን ችግራችሁ ምንድን ነው? እስቲ ንገሩን " የሚል መልስ ሰጡ። ወዲያው በንቦቹ መጣደፍ ውስጥ ውስጡን የተናደደችው አንዷ ዝንብ ወደፊት ቀረብ አለችና "መቼም ጉዳያችንን በዚህ በነፋስ ውስጥ መናገሩ ምስጢር መበተን ነው። ቢሆንም እናንተ ከቸኮላችሁብን ምን ይደረግ እንከተላችኋለን" አለች።




"ምን ሆናችሁ? ምን በደል ደረሰባችሁ? እስቲ ንገሩን ግዴለም?" አለች አንዷ ንብ። ከፊት በኩል የሚበረው ዝንብ ብስጭትጭት ብሎ "እኛ ዝንቦች ስንባል ያልደረሰብን ምን በደል አለ? ሰዎች እቤታቸው በገባን ወይም ዕቃቸው ላይ ባረፍን ቁጥር ያባርሩናል። በነፍሳት መግደያ አየሩን እየበከሉት ሳናስበው ይጨርሱናል። በዚህ አይነት እስካሁን ያለቀው የዝንብ ዘር ስፍር ቁጥር የለውም። ስንት ታላላቅና ደፋር የሆኑ ዝንቦች እንደ ቅጠል ረገፉ! ስንት የዝንብ ቆነጃጅት ያለ ርህራሄ ታፍነው ተገደሉ! ሌላው ቢቀር አዛውንት እንኳ ጭራ እያወናጨፉ ሸባ አድርገው ያስቀሯቸው ስንት የዝንብ እመቤቶች አሉ! ከዚህ የከፋ ምን በደል አለ!" ብሎ እንባ እየተናነቀው ተናገረ።

ወዲያው ሌላው ዝንብም ከተል አድርጎ "እኔ እኮ የምለው ሰዎች እኛን ለምን ጠሉን? "ጥዝ" እያልን ስለምንበር እረብሸናቸው ነው እንዳንል እንዲያውም የናንተ ድምፅ ከእኛ ያይላል። በዚህ ላይ እኛ እንደ እናንተ አንናደፍ። ሰዎች ግን ምን እንደታያቸው አናውቅም። ሁሌ እናንተን እያደነቁ እኛን ብቻ ያጠቁናል። የሚነፉብን የነፍሳት መግደያ መርዝ ገና ከሩቅ ሲሸተን "ኡሁ ኡሁ " ያስብለናል። ከዚያም ያቃጥለንና እንሞታለን። እናንተን ግን ቢበዛ ጢስ ነው የሚያጥኗችሁ። ይህንን የሚያደርጉትም ለጊዜው ቀፎአችሁን እንድትለቁላቸው ነው እንጂ ሊገድሏችሁ ብለው አይደለም። ማራችሁን ቆርጠው ጢሱን ሲያጠፉት ምንም ሳትሆኑ ወደ ቀፏችሁ እንደገና በሠላም ትመለሳላችሁ..." በማለት ምሬቱን ለንቦቹ ገለጸ።

ከንቦቹ አንዷ ወደ ዝንቦቹ ዞር ብላ ሰዎች ለምን ይጠሉናል? ለምንስ ጥምድ አርገው ያዙን ነው የምትሉት አይደለም?" ስትል ጠየቀቻቸው። በዚህ ጊዜ ሁለቱም ዝንቦች "አዎ" በማለት ጮክ ባለ ድምፅ መልስ ሰጡ። "እንግዲያውስ ለምን እንደሚጠሏችሁ ማስረዳቱ ቀላል ነው። ለመሆኑ አሁን የምትመጡት ከየት ነው?" ብላ ንቢቱ ጠየቀች። አንዷ ዝንብ "እወዲያ ማዶ ካለው የቆሻሻ መጣያ " ስትል መለሰች። "ከዚያስ በፊት የት ነበራችሁ?" ንቢቱ ድጋሚ ጠየቀች ። "ከዚያ በፊትም እታች አንድ የሞተ ከብት ነበረ እሱን ቀማምሰን ሳንጠግብ አሞራዎች አባርረውን ከመንደር አቅራቢያ መፀዳጃ ቤትም ጎራ ብለን ነበር..." ብላ ሁለተኛዋ ዝንብ በኩራት መንፈስ መለሰች።

"ታዲያ አሁን ወዴት ነው የምትሄዱት?" ንቢቱ አሁንም ጠየቀች። አሁንም ይኸው አብረን አይደል ወደላይኛው መንደር የምንሄደው? እያወቅሽ እንዴት ትጠይቂኛለሽ?" አለች ከፊት ያለችው ዝንብ። "ታዲያ ከቆሻሻ መጣያ ከጥንቡና ከሽንት ቤቱ ነካክታችሁ የያዛችሁት ቆሻሻ እላያችሁ ላይ ሆኖ እቤታቸው ድረስ ስትሄዱ እንዴት አይጠሏችሁ? እናንተ የምትውሉት ከመጥፎ ቦታ ነው። እኛ የምንውለው ግን ከጥሩ ቦታ ነው። እናንተን አጥቅተው እኛን ቢያደንቁ ያስከፋልን?" ብላ አንዷ ንብ ተናገረች።

ወዲያው ደግሞ አንዷ ዝንብ ቆጣ አለችና "እናንተ ከየት ነው የምትመጡት?" ስትል ንቦቹን ጠየቀቻቸው። "እኔ የምመጣው ከወንዝ ውሃ ቀድቼ እሷ እህቴ ደግሞ ለማር የሚሆን የጽጌረዳ አበባ ብናኝ ከአበቦች ላይ ቀስማ ነው" ስትል ንቢቱ መለሰች። "እንግዲያው እንደ እናንተ ጥሩ ነገር ካለበት ቦታ ብንውልና መልካም ብንሠራ ሰዎች ይወዱናል ማለት ነው?" ብላ ዝንቧ በድጋሚ ጠየቀች። "አዎ!" አሉ ንቦቹ በአንድነት። "ይህንን ባናደርግስ? ሌላ መፍትሔ የለውም ማለት ነው?" ዝንቦቹ ወደኋላ ቀረት ብለው ጠየቁ። ይኸን ጊዜ ንቦቹ "ይህን ባታደርጉማ የሰው ልጅ ጠላት ተብላችሁ እናንተን ይጨርሷችኋል።" ብለው ንቦቹ ፍጥነታቸውን ጨምረው ወደ ቀፏቸው በረሩ።

ልጆች ተረቱን ወደዳችሁት? እሺ ምን ተማራችሁ? ንጹሕ ቦታ መዋል ጥሩ እንደሆነ፣ ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር እንደማይገባ፣ ቅናት መጥፎ እንደሆነ፣ ከንቦች ታታሪነትን፣ ጥሩ ቦታ ሲዋል ሰዎች እንደሚወዱን፣ ለወሬ እና ለአሉባልታ ጊዜ መስጠት እንደማይገባ እና ሌሎችም አላችሁ አይደል? በጣም ጎበዞች። ልጆችዬ በሚቀጥለው ሳምንት እናንተ የምትማሩበትን ነገር ለማቅረብ ቃል በመግባት እና በቸር እንድንገናኝ በመመኘት በዚሁ ተሰናበትን።